# በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ (Adult Adoption) የመፍቀድ አስፈላጊነት፡- አንዳንድ ነጥቦች ከሌሎች አገራት ሕግጋት ተሞክሮ

*ነጋ እውነቴ መኮንን*[*]

## አኅጽሮተ ጥናት

*ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሮማዊያንን ሕግ ጨምሮ በጥንታዊ ሕግጋት ውስጥ ቦታ የነበረው ሲሆን ለአህጉረ አውሮፓና ለኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት በሆነው እ.አ.አ. በ1804 ዓ.ም በወጣው የፈረንሳዩ የናፖልዮን ሕግ እውቅና ተሰጥቶታል። እንዲሁም በሂደት በናፖልዮን ሕግ አማካይነት በዘመናዊው የፈረንሳይ፣ የእስፔን፣ የጣልያን፣ የጀርመንና በሌሎች የአውሮፓ አገራት ሕግጋት ውስጥ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የተፈቀደ ሲሆን፣ ከዚያም አልፎ በአሜሪካ ግዛቶችና በሌሎች የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በሚከተሉ አገራት የቤተሰብ ሕግጋት ውስጥ በስፋት እየተሠራበት ይገኛል። በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ትውፊታዊና ማኀበራዊ መሠረት የነበረው ሲሆን፣ ምንጩን በዋናነት ከፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ያደረገውና በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ለጉዳዩ እውቅና ከመንፈግ ባሻገር በወቅቱ ሥራ ላይ ከነበሩ ሌሎች ነባር የአገሪቱ የልማድ ሕግጋት ጋር አብሮ ሽሮታል፤ መሠረታቸውን የ1952 ዓ.ም የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ያደረጉትና በቀጣይ ተሻሽለው የወጡት የፌዴራልም ሆነ የክልል የቤተሰብ ሕግጋት ተመሳሳይ መንገድ ተከትለዋል። በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ የሚያስችሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ትውፊታዊ፣ ማኀበራዊና ሕጋዊ ምክንያቶች አሉ፤ በማለት ይህ አጥኝ ይከራከራል፤ እንዲሁም እነዚህን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ አሁን በሥራ ላይ ያለው የቤተሰብ ሕግ እንዲሻሻል አጥኚው ይመክራል።*

**ቁልፍ ቃላት፦** *ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ፣ የእድሜ ልዩነት፣ ቀደምት ግንኙነት፣ ባህላዊ፣ ትውፊታዊና ታሪካዊ መሠረት፣ ቤተሰባዊ፣ ማኀበራዊና ሥነ-ልቦዊ ምክንያቶች፣ የቤተሰብ ሕይወት የመከበር መብት*

## መግቢያ

ስለጉዲፈቻ ሲነሳ ወደ አእምሯችን የሚመጣው ሃሳብ የተለመደውና የታወቀው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ ነው። የኢትዮጵያን የቤተሰብ ሕግ ጨምሮ የሌሎች ብዙ አገራት የቤተሰብ ሕግጋት የህጻናት መብት ኮንቬንሽንም ጭምር የሚደነግጉት ይህንን

---

[*] በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት የሕግ ረዳት ፕሮፌሰር። ኤል ኤል ቢ.(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ1996 ዓ.ም)፣ ኤል ኤል ኤም (ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ግሮኒንገን፣ ዘኔዘርላንድስ በ2000 ዓ.ም)፣ ከፍተኛ ዲፕሎማ በማስተማር ሥነ-ዘዴ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2007 ዓ.ም)፣ የፒ ኤቹ ዲ ተማሪ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ)፤ ፀሀፊውን በኢ-ሜይል አድራሻው beleteeng@yahoo.com ማግኘት ይቻላል።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻን (child adoption) ነው፡፡[1] የዚህ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ መሠረታዊ አላማም በተለያየ ምክንያት ከወላጆቻቸው ጋር ማደግ ላልቻሉ ልጆች ሰው ሰራሽ በሆነ ዘዴ ወላጅ እንዲያገኙ በማድረግ ልጆችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ተግባሩ ከጥንት ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ የመጡት አገር አቀፍም ሆነ ዓለም ዓቀፍ ሕግጋት ጉዲፈቻው መደረግ ያለበት የልጁን/ጇን ጥቅም በሚጠብቅ መልኩ መሆን እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡

ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች የጉዲፈቻ አላማ ከተፈጥሮ ወላጆቻቸው ጋር ማደግ ላልቻሉ ልጆች ሰው ሰራሽ በሆነ መልኩ ወላጅ ማስገኘት በመሆኑ ጉዲፈቻ በአብዛኛው የሚፈቀደው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በተመለከተ ብቻ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚህ በታች በዝርዝር እንደምንመለከተው በአንጻሩ ጥንታዊና ታሪካዊ መሠረት ቢኖራቸውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህንን የጉዲፈቻ ተደራጊውን/ዋን እድሜ መሠረት ያደረገውን ቅድመ-ሁኔታና አስተሳሰብ የለወጡ ሕግጋት ብቅ እያሉ ነው፡፡ የእነዚህ ሕግጋት ዋና ማጠንጠኛ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጉዲፈቻ ከምናደርግበት አላማ የተለየ ቢሆንም ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችም ጉዲፈቻ እንዲደረጉ (adult adoption) መፍቀድ ነው፡፡[2] እንደሚታወቀው እንደሌሎች ውስን አገራት የቤተሰብ ሕግጋት የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ[3] የሚፈቅደው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻን ብቻ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ መደንገግና መፈቀድ እንደሚገባውና ከዚህም አኳያ በሥራ ላይ ያለው የቤተሰብ ሕግ መሻሻል እንዳለበት ከነምክንያቱ ማመላከት ነው፡፡ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን በሕግ የመደንገግ አስፈላጊነትን ለማሳየት የሌሎች አገራት የቤተሰብ ሕግጋት ተሞክሮዎች ይመረመራሉ፡፡ ከእነዚህ አገራት የቤተሰብ ሕግጋት ተሞክሮዎች የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ምን ይማራል? እንዴትስ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመን በቤተሰብ ሕጉ ውስጥ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ጉዲፈቻን ማካተት እንችላለን? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችና ነጥቦች በጥናቱ ይቃኛሉ፤ ይተነተናሉ፡፡ ጥናቱ በዋናነት ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ጉዲፈቻ በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ የመደንገግና የመፍቀድ አስፈላጊነትን ከባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ የሕግ ወይም ሰብአዊ መብት ምክንያቶች ጋር በማያያዝ ይከራከራል፤ ከዚህም አኳያ በሥራ ላይ ያለው የቤተሰብ ሕግ እንዲሻሻል ይመክራል፡፡

ወደ ጥናቱ ይዘት ስንመጣ በመጀመሪያ ስለ ጉዲፈቻ ጠቅላላ ገለጻ የሚደረግ ሲሆን፣ የጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የጉዲፈቻ አላማ፣ ለአካለ መጠን ስለደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ

---

[1] *Conventioin on the Rights of the Child, adopted* and opened for signature, ratification and accession by General Assembly resolution 44/25 of 20 November 1989 (entered into force 2 September 1990, in accordance with article 49), art. 21

[2] ለበለጠ መረጃ Mandi Rae Urban, The History of Adult Adoption in California, 11 J. CONTEMP. LEGAL Issues 612 (2000) ይመልከቱ፡፡

[3] "የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ" የሚለው ሐረግ ለአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች እንዲያገለግል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የወጣውንና ሌሎች ክልሎች አጽድቀው ሥራ ላይ ያዋሏቸውን የቤተሰብ ሕግጋትን ጭምር ለማመላከት የገባ ነው፡፡ ይህንን ሐረግ አጥኚው የመረጠበት ምክንያት የብሔራዊ ክልሎች የቤተሰብ ሕግጋት በጉዲፈቻም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ ስለሆኑ እንጂ አንድ ብሔራዊ የቤተሰብ ሕግ በኢትዮጵያ በመኖሩ አለመሆኑን አጥኚው ለአንባቢያን ማስገንዘብ ይወዳል፡፡

ታሪካዊ አመጣጥ፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ በሌሎች አገራት ሕግጋት ውስጥ ያለው ቦታ፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አስፈላጊነትን በመደገፍና በመቃወም የሚነሱ ምክንያቶች፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ መለያ ባሕሪያት፣ እንዲሁም ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አስፈላጊነትና ፋይዳ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ፤ የሚሉ ዓበይት ነጥቦች በቅደም ተከተል ይቃኛሉ፤ይተነተናሉ። በመጨረሻም የማጠቃለያ ነጥቦችን በማንሳትና የመፍትሄ ሃሳቦችን በመጠቆም ጥናቱ ይቋጫል።

## 1. ስለጉዲፈቻ በጠቅላላው

በዚህ ክፍል ስለጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥና አላማ አጭር ቅኝት ይደረጋል።

### 1.1. የጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥና አላማ

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ልጆችን ከተፈጥሮ ወላጆቻቸው ወደ ሌላ ቤተሰብ ለመመሥረት ለሚፈልጉ፣ የፖለቲካ ኅብረት ለመፍጠር ለሚያስቡ፣ ንብረትን በውርስ ለማዛወር ለሚሹ፣ በጋብቻ መተሳሰር ለሚፈልጉና በእድሜ ለገፉ ጧሪ ለሚፈልጉ አዛውንቶች በጉዲፈቻ ማዛወር የተለመደ ነበር።[4] ጉዲፈቻ ማድረግ በግሪክ ግዛቶች፣ በቱቶናዊያን (የጀርመን ነገዶች)፣ በስሎቫንያ ሩስያዊያንና በፖላንዶች ዘንድ የተለመደ ነበር።[5]

የጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥን በተመለከተ ሁለት ዋና ጥንታዊ ሕግጋትን ማንሳት ተገቢ ነው። እነሱም የሮማዊያን ሕግና የባቢሎናዊያን ወይም የሀሙራቢ ሕግ ናቸው። አሁን በሥራ ላይ ያሉት ዘመናዊ የጉዲፈቻ ሕግጋት በሙሉ ማለት ይቻላል፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ምንጫቸው የሮማዊያን ሕግ ነው።[6] እንደ ሮማዊያን ሕግ ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ተጽእኖ ማሳደር ባይችሉም በተወሰነ መልኩ የፈርኦናዊያን ወይም የግብጽ፣ የግሪክ እንዲሁም የእብራይስጥ ሕግጋት ተጠቃሽ ጥንታዊ የጉዲፈቻ ሕግ ምንጮች ናቸው።[7] ከክርስቶስ ልደት በፊት እ.አ.አ. በ2285 ዓመተ ዓለም የተደነገገው የባቢሎናዊያን ወይም የሀሙራቢ ሕግ ከዘመናዊው የጉዲፈቻ ሕግጋት ጋር የሚቀራረብ ድንጋጌ ነበረው፤ "አንድ ሰው አንድን ልጅ ወስዶ እንደ ልጁ ካሳደገው ማንም ሰው ይህንን የመንከባከብና የማሳደግ መብቱን አይነጥቀውም።" በማለት ሕጉ ይደነግጋል።[8]

ወደ ሮማዊያን ሕግ ስንመጣ የጉዲፈቻ ጉዳይ ለጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው ብቻ የተተወ የግል ወይም የቤተሰብ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት የሚታይበትና ጠንካራ መዋቅር የነበረው ነው።[9] በሞግዚት አስተዳደር ስር የነበሩ ልጆች

---

[4] Bisha Eugena, Adoptioin in Ancient Times, https://cyberleninka.ru/article/n/adoption-in-ancient-times/viewer

[5] Leo Albert Huard, The Law of Adoption: Ancient and Modern, 9 Vand. L. Rev. 743 (1956).

[6] ለበለጠ መረጃ Jean-François Mignot, "Les adoptions en France et en Italie: une histoire compare du droit et des pratiques (xixe-xxie siècles)", Vol. 70), (2015/4) ይመለከቷል።

[7] Adoption in Virginia, 38 Va. L. Rev. 546 (1952).

[8] የሀሙራቢ ሕግ አንቀጽ 185፤ ይህ አንቀጽ በእንግሊዝኛው *If a man has taken a young child 'from his waters' to sonship and has reared him up no one has any claim against that nursling* በማለት ይደነግጋል።

[9] ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 7፣ ገጽ 545።

በጉዲፈቻ ሲተላለፉ በሕግ የተቀመጡ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው በፍርድ ቤት መረጋገጥ ሲኖርባቸው ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ ሲደረጉ በነገሥታቱ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡[10] ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የሌሎች አገራት ጥንታዊ የጉዲፈቻ ሕግጋት ቢኖሩም ለአውሮፓውያን የጉዲፈቻ ሕግ መሠረት የሆነው ይህ በጁስትንያን የዳበረው የሮማ ሕግ ነው፡፡[11] እንደ አብዛኞቹ ቀደምትና ጥንታዊ ሕግጋት የሮማዊያን ሕግ ሴቶችን በተመለከተ አድሎአዊ ስለነበር ጉዲፈቻ ማድረግ የሚፈቀድላቸው ወንዶች ብቻ ነበሩ፡፡[12] ለዚህም ምክንያቱ በሮማዊያን ሕግ ቤተሰብን የመምራት መብት (*patria potestas)* የተሰጠው ለወንዶች ብቻ ስለነበረ ነው፡፡[13] ይህ ሕግ በሂደት ተሻሽሎ ውስን የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎች ሲሟሉ (ለምሳሌ አንዲት እናት ሁሉንም ልጆቿን በሞት ካጣች) ሴቶች ጉዲፈቻ የሚያደርጉበት ሁኔታ እየተፈጠረ መጣ፡፡[14]

የሮማዊያን ሕግ ለአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሎው የጉዲፈቻ ሕግ ላይ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ይህ ተጽእኖ ካረፈባቸው አገራት መካከል የፈረንሳይ ሕግ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡[15] በፈረንሳይ ሕግ በግልጽ የተቀመጡና በሂደት የዳበሩ ሁለት የጉዲፈቻ አይነቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ሙሉ (full) ጉዲፈቻ የሚባለው ሲሆን፣ ይህ የጉዲፈቻ አይነት እውቅና የተሰጠው እ.አ.አ. በ1939 እና በ1966 ዓ.ም በወጡት ሕግጋት ነው፡፡[16] በዚህ የጉዲፈቻ አይነት የሚካተቱት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወላጆቻቸውን በሞትና በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ልጆች ሲሆኑ፣ አላማውም ልጆቹን ከተፈጥሮ ወላጆቻቸው ጋር ያላቸውን ዝምድናና የሕግ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ የሚያቋርጥ ነው፡፡[17] ሁለተኛው ቀላል (simple) የሚባለውና እ.አ.አ. በ1804 እና በ1966 ዓ.ም በወጡት ሕግጋት እውቅና የተሰጠው ነው፡፡ ከሙሉ ጉዲፈቻ በተለየ የዚህ ጉዲፈቻ አላማ፣ ጉዲፈቻ ለሚደረገው ከተፈጥሮ ወላጆቹና ዘመዶቹ ተጨማሪ የጉዲፈቻ ወላጅና ዘመድ እንዲያገኝ ማስቻል ነው፡፡ ሁለተኛው የቀላል ጉዲፈቻ ባሕርይ፣ ከሙሉ ጉዲፈቻ በተለየ ጉዲፈቻ የሚደረጉት ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ብቻ መሆናቸው ነው፤ አላማውም ሃብትንና ንብረትን በውርስ ማስተላለፍ ነው፡፡[18]

የሮማ ሕግ እንደ ጉዲፈቻ የሕግ ምንጭ ያገለገለው ለአህጉረ አውሮፓ የሕግ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን፣ በዋናነት አሜሪካና እንግሊዝ ለሚካተቱበት የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትም ጭምር ነው፡፡[19] በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ጉዲፈቻን በተመለከተ ቀደም ሲል ምንም አይነት ሕግ ባለመኖሩ፣ በአሜሪካና በእንግሊዝ ይህንን ጉዳይ የሚደነግጉ የሮማ ሕግ ተጽእኖ ያረፈባቸው ሕግጋት ወጥተው ሥራ ላይ ውለዋል፡፡[20] እንግሊዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የጉዲፈቻ ሕግ ያጸደቀችው እ.አ.አ. በ1926 ዓ.ም ሲሆን በአሜሪካ ደግሞ ማሳቹሴትስ

---

[10] ዝኒ ከማሁ፡፡
[11] ዝኒ ከማሁ፡፡
[12] Walter J. III Wadlington, Minimum Age Difference as a Requisite for Adoption, 1966 Duke L.J. 395 (1966).
[13] ዝኒ ከማሁ፡፡
[14] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 395-96።
[15] ለበለጠ መረጃ ሊዮ አልበርት ሁዋርድ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 5 ይመለከቷል።
[16] ለበለጠ መረጃ Frederique Dreifuss-Netter, Adoption and Medically Assisted Procreation under French Law, 1996 St. Louis-Warsaw Transatlantic L.J. 93 (1996) ይመለከቷል፡፡
[17] ለበለጠ መረጃ Jean-François Mignot. Simple Adoption in France: Revival of an Old Institution (1804-2007), Revue française de sociologie, Centre National de la Recherche Scientifique, (2016) ይመለከቷል፡፡
[18] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 1።
[19] Jullian Bamberger, Adoption in Indiana, *Indiana Law Journal*, Vol. 17, Iss. 3, 225 (1941-42).
[20] ለበለጠ መረጃ ሊዮ አልበርት ሁዋርድ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 5 ይመለከቷል።

እ.አ.አ. በ1851 ዓ.ም የጉዲፈቻ ሕግ ደንግጋ ሥራ ላይ ያዋለች የመጀመሪያዋ ግዛት ናት። በመሆኑም የሮማ ሕግ በጥቅሉ እንዲሁም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዳበረው የናፖሊዮን ሕግ በተለይ ከአህጉረ አውሮፓ በተጨማሪ ለኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የጉዲፈቻ ሕግ ምንጭ ሆነው ከማገልገላቸውም በላይ ቀደምትነት የነበራቸውና ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሕግጋት መሆናቸውን እንገነዘባለን።

እንደ ሮማዊያን ሁሉ በጥንታዊ ግሪክም ጉዲፈቻ ተገቢ ቦታ ነበረው። በአቴንስ የነበረውን የጉዲፈቻ ሕግ ስንመለከት በዚህ ዘመን እየተሰራበት ካለው ሕግ በተቃራኒው ጉዲፈቻ የሚደረጉት ልጆች ሳይሆኑ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ነበሩ።[21] የዚህም ዋነኛ ምክንያት የጉዲፈቻ አላማና ጠቀሜታው ጉዲፈቻ የተደረገውን ሰው በቀጥታ ለመጥቀም ሳይሆን የጉዲፈቻ አድራጊውን ሃብትና ንብረት ወራሽ እንዲኖረው በማድረግና የዘር ሐረጉን በማስቀጠል ላይ ያተኮረ በመሆኑ ነበር።[22]

ጥንታዊያኑን የሮማና የግሪክ የጉዲፈቻ ሕግጋት ከሌሎች ሕግጋት የሚለያቸው ነገር ቢኖር ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን የደነገጉና የፈቀዱ መሆናቸው ነው።[23] ከዚህ በታች እንደምንመለከተው ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አላማ ጉዲፈቻ አድራጊውን ለመጥቀም ቢሆንም በጥንታዊት ሮማ ለአካለ መጠን የደረሱ ነጻ ሰዎችን ጉዲፈቻ ማድረግ የተለመደ ነበር።[24]

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥ ጀምሮ እንደምንገነዘበው ዋናው የጉዲፈቻ አላማ ጉዲፈቻ ተደራጊውን ሳይሆን የጉዲፈቻ አድራጊውን ጥቅም ለመጠበቅ ነበር። እንደ ሮማ ባሉ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ጉዲፈቻ ከጉዲፈቻ አድራጊው ጥቅም በተጨማሪ ፖለቲካዊና አገራዊ ፋይዳ ጭምር ነበረው።[25] ለምሳሌ የሮማ ነገሥታት ቀጣይ የዙፋናቸው ወራሽ እንዲኖር ለማረጋገጥ ጉዲፈቻን እንደ አማራጭ ይጠቀሙበት ነበር።[26]

## 1.2. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥ በአጭሩ

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ መቼ ተጀመረ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ቢያስቸግርም ከጥንት ጀምሮ የተፈጥሮ ልጅ የሌላቸው ሰዎች በእድሜ ለሚበልጡት ጓደኛ ሃብትንና ንብረትን በውርስ ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት አይነተኛ መሣሪያ ነበር።[27] ነገር ግን የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ በተመለከተ እርግጠኛ ሆኖ መናገር

[21] Nigel Wilson (ed.), Encyclopedia of Ancient Greece, 10 (2013)

[22] ዝኒ ከማሁ።

[23] Adult Adoption, 1972 Wash. U. L. Q. 254 (1972) በጥንታዊያኑን በግሪክና በሮማ የጉዲፈቻ ሕግጋት መካከል ያለውን ንጽጽር ይበልጥ ለመረዳት Hugh Lindsay, Adoption in Greek Law: Some Comparisons with the Roman World, *New Castle Law Review*, Vol. 3, No. 2, 1999 ይመለከቷል።

[24] Hugh Lindsay, Adoption in Greek Law: Some Comparisons with the Roman World, 3 Newcastle L. REV. 91 (1999).

[25] C. D. Spinellis and C. Shachor R-Landau, Reflections on the Law of Adoption in Greece and Israel in Light of the European Convention, *Revue Hell6nique de Droit International,* Vol. 25, 1972, p. 144

[26] ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 7፣ ገጽ 545።

[27] Russell E. Jr. Utter, The Benefits and Pitfalls of Adult Adoption in Estate Planning and Its Likely Future in Missouri, 80 UMKC L. Rev. 256 (2011).

የሚቻለው ለአካለመጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በጥንታዊቷ ሮማ እንደተጀመረ ነው።[28] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ማለት ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው ከመደበኛው ጉዲፈቻ ሥርዓት በተለየ በአንድ አገር የፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት አንድ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ሌላ ለአካለ መጠን የደረሰን ሰው በጉዲፈቻ ተቀብሎ ልጁ የሚያደርግበት ሥርዓት ማለት ነው።[29]

ልክ እንደ መደበኛው ጉዲፈቻ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ መሠረቱና ታሪካዊ አመጣጡ በዋናነት የምዕራብ አገራት ባህልና ሕግ ነው።[30] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ቀደምት የሕግ እውቅና ካገኙባቸው የሕግ ሥርዓቶች መካከል የሮማዊያን ሕግ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሲሆን ሕጉ መደበኛውን ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻና ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለያይቶ የሚደነግግ ነበር። መደበኛው ጉዲፈቻ በሞግዚት ስር ያሉ ልጆች በጉዲፈቻ የሚተላለፉበት አሠራርን ሲያመለክት፤ ለአካለመጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ደግሞ ከሞግዚት ነጻ የነበሩ ሰዎች የጉዲፈቻ ቤተሰብ የሚያገኙበትን ሥርዓት የሚደነግግ ነው። ይህ በሮማዊያን ዘንድ ሲሠራበት የቆየው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ አላማን በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን እነሱም ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ግንኙነትን ለመመሥረትና ሃብትንና ንብረትን በውርስ የማስተላለፊያ መንገድ ሆኖ ማገልገሉ ናቸው።[31]

ይህ አሠራር ከጥንታዊያኑ የግሪክና የሮማዊያን ስልጣኔ ጀምሮ የአውሮፓ አገሮችን አካሎ የአትላንቲክ ውቅያኖስን ተሻግሮ እስከ ዘመናዊቷ አሜሪካ ድረስ የዘለቀ ነው። ጉዳዩን ከሌሎች የምእራብ አገራት ይልቅ በአሜሪካ ልዩ የሚያደርገው ይህ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከመደበኛው ጉዲፈቻ ጋር በተቀራራቢ ጊዜ የሕግ እውቅና ማግኘቱ ነው።[32]

## 2. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አስፈላጊነትን በመደገፍና በመቃወም የሚነሱ መከራከሪያዎች

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በሕግ ተፈቅዶ ሥራ ላይ በዋለባቸው አገራት ጥቅሙንና ጉዳቱን አስመልክቶ በፀሀፍት የተለያዩ ሃሳቦች ይሰነዘራሉ። በጥናቱ መግቢያ እንደተመለከተው የዚህ ምርምር ዋናው አላማ በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ መፈቀድ አለበት የሚልና ለዚህም አሳማኝ ምክንያቶችን ማመላከት ቢሆንም አሁን ያለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ተሻሽሎ ወደ ሥራ ቢገባ በሌሎች አጋራት ሕግጋት ያጋጠሙ ችግሮች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ችግር መሆን አለመሆናቸውን መመርመር እንዲሁም ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሚኖሩትን አንጻራዊ ጥቅሞችና ጉዳቶችን በአጭሩ መቃኘት አስፈላጊ ነው።

---

[28] ዝኒ ከማሁ።

[29] ለበለጠ መረጃ https://legaldictionary.net/adult-adoption/ ይመለከቷል።

[30] Robert Keefe, Sweet Child O' Mine: Adult Adoption & Same-Sex Marriage in the Post-Obergefell Era, 69 Fla. L. Rev. 1481(2017).

[31] ዝኒ ከማሁ።

[32] ዝኒ ከማሁ።

### 2.1. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አስፈላጊነትን በመደገፍ የሚነሱ መከራከሪያዎች

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በመደገፍ የሚነሱ ክርክሮችና ምክንያቶች በአብዛኛው ጉዳዩ በሕግ ተፈቅዶ ሥራ ላይ ያዋሉ አገራትን ተሞክሮና የሕግ አውድ መሠረት ያደረጉ ናቸው። እነዚህን ክርክሮችና ምክንያቶች መመልከት በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ቢፈቀድ ምን ምን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል? የሚለውን ለመመዘንና ለመመርመር ያግዛል። ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በመደገፍ በብዙ ፀሀፍት የተለያዩ የመከራከሪያ ነጥቦች ይቀርባሉ። በጉዳዩ ላይ የጻፉ ምሁራን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በመደገፍ የሚከተሉትን ክርክሮች ያነሳሉ፦

1) ጉዲፈቻ አድራጊው ጉዲፈቻ ማድረግ የፈለገው ሰው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሆኖ እያለ ጉዲፈቻ ማድረግ ፈልጎ ይህ ፍላጎቱ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካ ሲቀር፣
2) ልጅ የሌላቸው ባልና ሚስት ወይም ልጅ የሌለው ሰው የቤተሰብ ስሙን ማስቀጠል ሲፈልግ፣ ወይም አንደኛው የትዳር አጋር ቢሞት ረዳትና ደጋፊ ለማግኘት፣
3) ጉዲፈቻ አድራጊው ጉዲፈቻ ማድረግ የፈለገውን ሰው በሂደት መቀራረብና ቤተሰባዊ ወዳጅነት መፍጠር፣ እንዲሁም
4) አንድ ሰው ለአካለ መጠን የደረሰ የእንጀራ ልጁን ጉዲፈቻ ማድረግ ቢፈልግ የሚሉ ሲሆን፤[33] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በዋናነት ቀድሞ የነበረን ቤተሰባዊ ግንኙነት ሕጋዊ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በተለይ በአሜሪካ በእንጀራ አባት/እናት እና በእንጀራ ልጅ መካከል የነበረን ቀደምት ግንኙነት ወደ ልጅና ወላጅ ግንኙነት ለመለወጥ ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል።[34]
5) ሌላው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ጥቅም ጉዲፈቻ አድራጊው ወይም ተደራጊው ሲሞት ሃብት ንብረትን በውርስ ለማስተላለፍ ማስቻሉ ነው።[35] እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ ከውርስ ውጪ ሀብት ንብረትን በሌሎች ሕጋዊ መንገዶች ማለትም በኑዛዜና ከሞት በኋላ በሚፈጸም ስጦታ ማስተላለፍ ስለሚቻል ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ አስፈላጊ አይደለም የሚል ሲሆን እነዚህ የሀብትና ንብረት ማስተላለፊያ መንገዶች ከሚቹ የሥጋ ዘመዶች በተለያየ መልኩ ጥያቄና ተቃውሞ ሊቀርብባቸው ስለሚችል ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ተመራጭ ያደርገዋል።[36]

እነዚህን የመከራከሪያ ነጥቦች ወይም ምክንያቶች በሁለት ከፍሎ ማየት የሚቻል ሲሆን እነሱም የልጅና የወላጅ ግንኙነት ያለበት እና የልጅና የወላጅ ግንኙነት የሌለበት ናቸው።[37] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በመደገፍ የሚነሱ ምክንያቶች በጥቅሉ ሲታዩ በአንድ መሠረታዊ ነጥብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይኸውም በጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው መካከል ቀድሞ የነበረንና በተለያዩ ምክንያቶች የተመሠረተ ግንኙነትን ተጠናክሮ

[33] Walter Wadlingtont, Adoptioin of Adults: A Family Law Anomality, 54 Cornell L. Rev. 578 (1968-1969)
[34] ሮበርት ኪፊ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 30፣ ገጽ 1482::
[35] Gwendolyn L. Snodgrass, Creating Family without Marriage: The Advantages and Disadvantages of Adult Adoption among Gay and Lesbian Partners, 36 Brandeis J. FAM. L. 81 (1997).
[36] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 81-82።
[37] ዋልተር ዋድሊንገተን፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 33፣ ገጽ 578።

እንዲቀጥል (solidify) በማድረግ በመጨረሻ የጉዲፈቻ ልጁን ወራሽ እንዲሆን ማስቻል ነው።[38]

## 2.2. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ አስፈላጊነትን በመቃወም የሚነሱ መከራከሪያዎች

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሚነቀፍበት አንዱ ምክንያት ቀድሞ በሕግ ያልተፈቀደና ሕጋዊ ያልሆነን በጉዲፈቻ አድራጊውና ጉዲፈቻ ተደራጊው መካከል የነበረን ድብቅ ግንኙነት ወይም የጎንዮሽ ዓላማን በጉዲፈቻ ሽፋን ለማስቀጠል መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል ወይም በእንግሊዝኛው collateral purpose ይኖረዋል የሚል ነው። ይህ መከራከሪያ በዋናነት የሚነሳው ከተመሳሳይ ጾታ ጾታዊ ግንኙነት ወይም ግብረ-ሰዶማዊያን ጋር ተያይዞ ነው።[39] እንደ አሜሪካ ባሉ አገራት የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ በሕግ ከመፈቀዱ በፊት ጾታዊ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በማድረግ ግንኙነቱን ለማኅበረሰቡ የአባትና የልጅ ወይም የእናትና የልጅ አስመስሎ ማቅረብ የተለመደ ነበር።[40] ይህ በግብረ-ሰዶማዊያን የሚደረግ ጉዲፈቻ በሕግ ያልተፈቀደን የተመሳሳይ ጾታ ሃሳዊ ጋብቻ (pseudo-marriage) ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት ያገለግላል ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ ልጅና ወላጅ መስለው ከመታየት ባለፈም ጉዲፈቻን ሃብት ንብረታቸውን በውርስ ለማስተላለፍ አይነተኛ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙበታል።[41]

የዚህ ክርክር መነሻ በዋናነት ለታችኞቹ የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ሲቀርቡ የነበሩ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች የጉዲፈቻ ጥያቄ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ሕጋዊነት ላይ እ.አ.አ. በ2015 ዓ.ም ህጋዊ ነው በሚል ከሰጠው ውሳኔ ጋር ተያይዞ ጉዳዩ ለአሜሪካ ሕግጋትና ፍርድ ቤቶች የሕግ ክርክር የሚያስነሳ አይደለም።[42] ጉዳዩን ይበልጥ ለማብራራት የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ሕጋዊ ከመሆኑ በፊት ከተሰጡ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ውስጥ ለኒውዮርክ ከተማ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎት ቀርቦ የነበረን ጉዳይ በአጭሩ እንመልከት። የጉዲፈቻ ማመልከቻው ለፍርድ ቤቱ የቀረበው እ.አ.አ. በ1982 ዓ.ም ሲሆን፣ የ57 ዓመት እድሜ የነበረው ሰው ለ25 ዓመታት ጥብቅ የሥራና የግል ግንኙነት የነበረውን የ50 ዓመት ጎልማሳ ጉዲፈቻ ለማድረግ የቀረበ ማመልከቻ ነው። ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ለውሳኔው በምክንያትነት የቀረበው አመልካቶች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሚፈቅደውን ሕግ የተመሳሳይ ጾታ ሃሳዊ ጋብቻ ለመፈጸም በሽፋንነት ተጠቅመውበታል የሚል ነው።[43] ነገር ግን በአሜሪካ የታችኞች ፍርድ ቤቶች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ነበረው

[38] Thomas Adolph Pavano, Gay and Lesbian Rights: Adults Adopting Adults, 2 Conn. Prob. L.J. 261-262 (1987).

[39] Brynne E. McCabe, Adult Adoption: The Varying Motives, Potential Consequences, and Ethical Considerations, 22 Quinnipiac Prob. L.J. 301 (2009).

[40] ለበለጠ መረጃ Peter N. Fowler, Adult Adoption: A New Legal Tool for Lesbians and Gay Men, 14 Golden Gate U. L. Rev. (1984) ይመለከቷል።

[41] In re Robert P., 117 Misc. 2d 279, 458 N.Y.S.2d 178 (1983), aff'd mem. sub nom. In re Pavlik, N.Y.L.J., Nov. 17, 1983, at 6, col. 3 (N.Y. App. Div.) (court denied an adoption petition on the basis that the parties were attempting to create a pseudo-marriage through use of the adult adoption statute), ፒተር ኤን ፋውለር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 40፣ ገጽ 669 ይመለከቷል።

[42] Obergefell v. Hodges, 576 U. S. ____ (2015)

[43] ለበለጠ መረጃ ፒተር ኤን ፋውለር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 40 ይመለከቷል።

ይህ ምክንያት በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው ይሻር ነበር።[44] ምንም እንኳ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ጋር ተያይዞ የተመሳሳይ ጾታ ሃሳዊ ጋብቻ ክርክር ቢነሳም ጉዲፈቻው በማጭበርበር ወይም በአላስፈላጊ ተጽእኖ ካልተደረገ በስተቀር ሊሰረዝ ስለማይችል (irrevocable በመሆኑ) ጉዳዩ ለግብረ-ሰዶማዊያን አይነተኛ አማራጭ ሆኖ አያውቅም።[45] ድብቁ የተቃራኒ ጾታ ጾታዊ ግንኙነቱና መፈላለጉ በሂደት ሊቀር ቢችል በሕግ የሚታወቀው የጉፈቻው ግንኙነት ሊሰረዝ ስለማይችል በአብዛኛው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ለሃሳዊ ጋብቻ በሽፋንነት ጥቅም ላይ ሲውል አይታይም።[46]

ከተመሳሳይ ጾታ ጉዳይ ጋር የሚመሳሰለውና ሌላው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የመቃወሚያ ነጥብ በተቃራኒ ጾታ የፍቅር ግኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ልክ እንደተመሳሳይ ጾታ ጾታዊ ግንኙነት ድብቅ የፍቅር ግንኙነት ያላቸው አንድ ወንድና ሴት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በማድረግ ግንኙነታቸውን የልጅና ወላጅ አድርጎ ለማቅረብ እንደ ሽፋን ይጠቀሙብታል የሚል ነው።[47] ብዙውን ጊዜ ከዚህ የተቃራኒ ጾታ የፍቅር ግኙነትና ጉዲፈቻ በስተጀርባ ያለው ምክንያት በዋናነት የፍቅር ግኙነቱ እንዳይታወቅ መፍራት ሳይሆን ሃብትንና ንብረትን በውርስ ከማስተላለፍ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ጉዳይ በቀጥታ ሊያያዝ የሚችለው ከውርስ ሕግ ጋር ሲሆን ባል የሚስቱ፣ እንዲሁም ሚስት የባሏ ወራሽ ባልሆነችበት አገር (jurisdiction) ይህንን የሕግ ክልከላ የልጅና የወላጅ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችለውን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በሽፋንነት በመጠቀም ማምለጥ ይቻላል ማለት ነው። በመሆኑም ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ይህን የመሳሰሉ ኢሞራላዊና ግብረ-ገብነት የጎደላቸውን ግንኙነቶች ለመሸፈንና ለማስቀጠል መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፤ የሚለው አንዱ የሚነቀፍበት ምክንያት ነው።

## 3. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ በሌሎች አገራት ሕግጋት ውስጥ ያላቸው ቦታና ታሪካዊ መሠረት

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ውስጥ መፈቀድ አለበት የሚለውን ጉዳይ ከመመልከታችን በፊት ጉዳዩ በሌሎች አገራት ሕግጋት ውስጥ ምን ቦታ አለው፤ የሚለውን ጉዳይ መቃኘቱ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ በዚህ ክፍል ስር በአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓትና በኮመን ሎው ሕግ ሥርዓት ውስጥ ያሉ አገራት በምን መልኩ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ እየሰሩበት ይገኛሉ የሚለውን እንቃኛለን።

ከአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓት የፈረንሳይ፣ የጣልያንና የጀርመን ሕግጋቶችን የምንመለከት ሲሆን፤ የአሜሪካና እንግሊዝ ሕግጋት ደግሞ ከኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የሚዳሰሱ ይሆናሉ። እነዚህ አገራት የተመረጡበት ዋናው ምክንያት ለጉዳዩ የሰጡትን ትኩረት መነሻ በማድረግ ነው።

---

[44] Gwendolyn L. Snodgrass, Creating Family without Marriage: The Advantages and Disadvantages of Adult Adoption among Gay and Lesbian Partners, 36 Brandeis J. FAM. L. 81 (1997).
[45] Mandi Rae Urban, The History of Adult Adoption in California, 11 J. CONTEMP. LEGAL Issues 615 (2000).
[46] ዝኒ ከማሁ።
[47] ብሪን ኢ. ማኬብ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 39፣ ገጽ 301።

### 3.1. የአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓት

ከዚህ በላይ በጉዲፈቻ ታሪካዊ አመጣጥ ክፍል ስር እንደተጠቀሰው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከመደበኛው ጉዲፈቻ ጎን ለጎን መነሻውን የሮማውያንን ሕግ አድርጎ ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገራት እንደተስፋፋና ለኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የጉዲፈቻ መሠረት እንደሆነም አይተናል፡፡ በዚህ ክፍል ስር ጉዳዩ በአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓት ምን ቦታ እንደነበረውና እንዳለው ዘርዘር አድርገን እንመለከታለን፡፡

ፈረንሳይ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በሕግ ፈቅዳለች፡፡ በዚሁ መሠረት በዋናነት የሮማዊያን ሕግ ተጽእኖ ያረፈበት እ.አ.አ. በ1804 የወጣው የፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወይም እድሜያቸው ከሃያ አንድ ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ጉዲፈቻ እንዳይደረጉ ይከለክላል፡፡[48] ይህም የሆነው በዚህ ሕግ መሠረት አንድ ልጅ ለአካለ መጠን ደረሰ የሚባለው እድሜው ሃያ አንድ ዓመት ሲሞላው ነው፡፡[49] ጉዲፈቻ ለማድረግ ከዚህ በተጨማሪ ሕጉ ሁለት ቅድመ-ሁኔታዎችን ያስቀምጣል፡፡ የመጀመሪያው ቅድመ-ሁኔታ ከጉዲፈቻ አድራጊዎች እድሜ ጋር የተያያዘ ሲሆን ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ጉዲፈቻ ለማድረግ እድሜያቸው በትንሹ አምሳ ዓመት ሊሞላቸው ይገባል፡፡[50] ሁለተኛው ቅድመ-ሁኔታ ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ በጋብቻ ውስጥ የተወለደ ልጅ (legitimate child) የሌላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡[51] ይህ ቅድመ-ሁኔታ በዋናነት ጉዲፈቻው በውርስ ላይ የሚኖረውን ውጤትና የጉዲፈቻ አድራጊዎቹን ልጆች ጥቅም ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሁለተኛው ቅድመ-ሁኔታ እ.አ.አ. በ1976 ዓ.ም በተሻሻለው ሕግ እንዲቀር ተደርጓል፡፡[52]

ሁለተኛው ከፈረንሳይ የተቀዳው እ.አ.አ. በ1900 ዓ.ም የወጣው የጀርመን የፍትሐ ብሔር ሕግ ሲሆን ይህ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ፈቅዷል፡፡ ምንም እንኳ ይህ ሕግ ሁለቱንም አይነት ማለትም ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻን ቢፈቅድም ሕጉ በወጣበት የመጀመሪያው አስር አመታት ከፍተኛ ቁጥር የያዘው ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ ነበር፡፡[53] ይህም ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ በጀርመን ሕግ የተሰጠውን ቦታ ያሳያል፡፡

የሮማዊያን ሕግና የፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ተጽእኖ ያረፈበትና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ የፈቀደው ሦስተኛው ሕግ እ.አ.አ. በ1865 ዓ.ም የወጣው የጣሊያን የፍትሐ

[48] የሕጉን አንቀጽ 346 እና 388 ከሚከተለው ድረገጽ ላይ ይመለከቷል፤ http://files.libertyfund.org/files/2353/CivilCode_1566_Bk.pdf

[49] ዝኒ ከማሁ፡፡

[50] የሕጉን አንቀጽ 343 ከሚከተለው ድረገጽ ላይ ይመለከቷል፤ http://files.libertyfund.org/files/2353/CivilCode_1566_Bk.pdf

[51] ዝኒ ከማሁ፡፡

[52] Jean-Francois Mignot, Child Adoption in Western Europe, 1900–2015, in Cliometrics of the Family, Springer, 5 (2019).

[53] ዝኒ ከማሁ፡፡

ብሔር ሕግ ነው፡፡[54] በዚህ ሕግ መሠረት አስራ ስምንት ዓመት የሞላቸውና የወላጆቻቸውን ፈቃድ ያገኙ ሰዎች ጉዲፈቻ እንዲደረጉ ይፈቀድላቸዋል፡፡[55]

የናፖሊዮንን የፍትሐ ብሔር ሕግ ውስን ማሻሻያ በማድረግ ጣልያንንና ጀርመንን ጨምሮ ኔዘርላንድ እ.አ.አ. በ1838 ዓ.ም፣ ሮማንያ እ.አ.አ በ1865 ዓ.ም፣ ፖርቱጋል እ.አ.አ በ1867 ዓ.ም፣ እስፔን እ.አ.አ በ1888 ዓ.ም፣ እንዲሁም ስዊዘርላንድ እ.አ.አ 1912 ዓ.ም ተቀብለው የየአገራቸው ሕግ አድርገውታል፡፡[56] በዚህም ምክንያት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ጨምሮ የአብዛኛው የአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓት ተከታይ የሆኑ አገራት ከዚህ በላይ ከተመለከትነው ከፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን መገንዘብ እንችላለን፡፡ እነዚህ የተለያዩ አገራት ሕግጋት ከናፖሊዮን የፍትሐ ብሔር እንደመቀዳታቸው በወቅቱ ሲጸድቁ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ በዋናነት እንደምክንያት ተመልክቶ የነበረው ጉዲፈቻ አድራጊው የተፈጥሮ ልጅ የሌለው መሆኑ ነው፡፡[57]

### 3.2. የኮመን ሎው ሕግ ሥርዓት

የአህጉረ አውሮፓ የሲቪል ሕግ ሥርዓት ከጥንታዊ የሮማና የግሪክ ሕግጋት ጀምሮ በጁስቲንያን ከዚያም በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዳበረው የናፖሊዮን ሕግ አማካይነት ከሁለት ሺ አመታት በላይ የቆየ የጉዲፈቻ ሕግ እንዳለው ተመልክተናል፡፡ ወደ ኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ስንመጣ ግን የጉዲፈቻ ጉዳይ ከሌሎች ሕግጋት በተለየ በሕግ ሥርዓቱ ውስጥ ትኩረትና ቦታ ባለማግኘቱ በኮመን ሎው የዳበረ አልነበረም፡፡[58] በመሆኑም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የማሳቹሴትስ ግዛት እ.ኤ.አ. በ1851 ዓ.ም የጉዲፈቻ ሕግ ደንግጎ ሥራ ላይ እስኪያውል ድረስ በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት በአሜሪካም ይሁን በእንግሊዝ እንዲሁም የሕግ ሥርዓቱ ተከታይ በሆኑ ሌሎች አገሮች ምንም አይነት የጉዲፈቻ ሕግ አልነበረም፡፡[59] ይህ ሕግ የሮማውያን ሕግ ተጽዕኖ ያረፈበት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ምንም እንኳ የኮመን ሎው የጉዲፈቻ ሕግ መሠረቱ የሮማውያን ሕግ ቢሆንም ከዚህ በታች እንደምንመለከተው ሕጉን በመተርጎምና በመተንተን ፍርድ ቤቶች ለሕጉ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጾ አድርገዋል፡፡ በዚህ ክፍል ስር በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት ከሚጠቀሱት አገራት ዋና ዋናዎቹ ማለትም አሜሪካ እና እንግሊዝ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሰጡትን ቦታ እንቃኛለን፡፡

[54] ለበለጠ መረጃ ገርን ፈራንኮይስ ሚነት፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 6፣ ገጽ 761 ይመለከቷል፡፡

[55] ዝኒ ከማሁ፡፡ በዚህ የፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት አንድ ሰው ለአካለ መጠን እንደደረሰ የሚቆጠረው እድሜው ሃያ አንድ ዓመት ሲሞላው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ዝኒ ከማሁ፡፡

[56] ለበለጠ መረጃ Seldag Gunes Peschke, Legal Status of Turkish Women: Past and Present under the Turkish Civil ode, 7 Ankara B. Rev. 27 (2014) ይመለከቷል፡፡

[57] ለበለጠ መረጃ Child Adoption: Trends and Policies, Department of Economic and Social Affairs Population Division, United Natioins, New York, 2009 ይመለከቷል፡፡

[58] Hope C. Blain, I Now Pronounce You Husband and Son: Confronting the Need to Amend Adult Adoption Codes to Facilitate Same-Sex Marriage, 22 Chap. L. Rev. 411 (2019).

[59] Elizabeth J. Samuels, The Idea of Adoption: An Inquiry into the History of Adult Adoptee Access to Birth Records, 53 Rutgers L. Rev. 368 (2001).

### 3.2.1. አሜሪካ

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በአሜሪካ ግዛቶች ታሪክ የመጀመሪያዋ መደበኛውን ጉዲፈቻ በሕግ የፈቀደችው ግዛት ማሳቹሴትስ ስትሆን መደበኛው ጉዲፈቻ የሕግ እውቅና ካገኘ ከሃያ ዓመታት በኋላ የመጀመሪያውን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ግዛቷ ፈቅዳለች። በዚህ ጉዳይ ላይ ፈር ቀዳጅ እርምጃ ከወሰዱ የአሜሪካ ግዛቶች ሁለተኛዋ ግዛት ኢንዲያና ናት። ምንም እንኳ የኢንዲያና የጉዲፈቻ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በግልጽ ባይፈቅድም የግዛቷ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እ.አ.አ. በ1892 ዓ.ም ጉዳዩ ቀርቦለት "ልጅ" የሚለው ቃል ለአካለ መጠን ያልደረሱትን ብቻ ለማመላከት የሚያገለግል ቃል ሳይሆን የአንድ ሰው ልጅነት ለአካለ መጠን ሲደርስ የማይቀርና ከዚያ በኋላም የሚቀጥል በመሆኑ የጉዲፈቻ ሕጉ ለሁሉም ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆችና ለአካለ መጠን ለደረሱ ሰዎች እኩል ተፈጻሚ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም የሚል ትንተና በሕጉ ላይ ሰንዝሯል።[60] እ.አ.አ. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ተመሳሳይ ጉዳይ የቀረበለት የሚዙሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ ተመሳሳይ ትንታኔና ፍርድ ሰጥቷል።[61] ልክ እንደ ኢንዲያና የጉዲፈቻ ሕግ የሚዙሪ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን በተመለከተ ግልጽ ድንጋጌ ያልነበረው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ "ልጅ" የሚለው ቃል በሕጉ ምን ለማመላከት እንደገባ ትርጉም መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በአሜሪካም የቤተሰብ ሕግ የመደንገግ ሥልጣን የግዛቶች ስልጣን ቢሆንም ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ጨምሮ ስለ ጉዲፈቻ የአሜሪካ ወጥ ሕግ ኮሚሽን (U.S. Unifrorm Law Commission) እ.አ.አ. በ1994 ዓ.ም ለሁሉም ግዛቶች በሞዴልነት የሚያገለግል የጉዲፈቻ ሕግ (The Uniform Adoption Act) አውጥቷል።[62] በዚህ ሞዴል ሕግ መሠረት አንድ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ሌላ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ማድረግ እንደሚችል ፈቅዷል።[63] ይህ ሞዴል የጉዲፈቻ ሕግ አስገዳጅ ባለመሆኑ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ጨምሮ ሌሎች የሕጉን ክፍል ሙሉ በሙሉ የተቀበሉ እንደ ቬርሞንት ያሉ ግዛቶች ቢኖሩም ሊሎቹ ነባሩን የጉዲፈቻ ሕጋቸውን በተወሰነ መልኩ ክፍተት ለመሙላት ተጠቅመውበታል።[64]

ወደ ግዛቶች ሕግጋት ስንመጣ በአሁኑ ወቅት ሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ፈቅደዋል።[65] ምንም እንኳ ሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ቢፈቅዱም የሕግጋቱ አተገባበርና የሚያስቀምጡትን ቅድመ-ሁኔታ ግን በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን። የመጀመሪያው መንገድ የግዛቶቹ የቤተሰብ

---

[60] የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አመክንዮ በእንግሊዝኛ የሚከተለው ነው "It is also true that the word "child," as commonly used, carries with it the idea of tender years and of minority. It is, however, also true that one's child does not cease to be his child when it attains its majority... We see no reason why [the adoption statute] may not apply to adults equally with infants." ለበለጠ መረጃ ራስል ኢ. አተር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 27፣ ገጽ 257 ይመለከቷል።

[61] ዝኒ ከማሁ።

[62] ይህ ኮሚሽን በጉዲፈቻ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ጉዳዮች ላይም አስገዳጅ ያልሆኑ ሞዴል ሕግጋትን ያወጣል፤ እነዚህን ሞዴል ሕግጋትን በሕጋቸው ውስጥ ማካተት የግዛቶቹ ምርጫና ስልጣን ነው።

[63] UNIF. ADOPTION ACT § 5-101

[64] ብራን ኢ. ማኬብ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 39፣ ገጽ 304::

[65] ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ድረገጽ ይመለከቷል፤ https://adoptingback.com/adopting-back/united-states-adult adoption-law/

ሕግጋት ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን በግልጽ የሚፈቅዱበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጉዳዩ በዝምታ ሲታለፍ የሕግ አውጪው ፍላጎት ምን እንደሆነ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትርጉም ነው፡፡[66] የመጀመሪያውን መንገድ ከተከተሉ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ አላባማ፣ አላስካ፣ አሪዞና፣ አርካንሳስ፣ ካሊፎርንያ፣ ኮሎራዶ፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት፣ ፍሎሪዳ፣ ጆርጂያ፣ ሃዋይ፣ ኢሊኖይስ፣ ካንሳስ፣ ኬንታኪ፣ ሉዚያና፣ ሜሪላንድ፣ ማሳቹሴትስ፣ ሚቺጋን፣ ሚኖሶታ፣ ሚሲሲፒ፣ ሚዙሪ፣ ሞንታና፣ ኔብራስካ፣ ኔቫዳ፣ ኒው ጀርሲ፣ ኒው ሜክሲኮ፣ ኒው ዮርክ፣ ኖርዝ ካሮላይና፣ ኖርዝ ዳኮታ፣ ኦሀዮ፣ ኦክላሆማ፣ ኦሪጎን፣ ፔኒሲሊቫኒያ፣ ሮዴ አይላንድ፣ ሳውዝ ካሮላይና፣ ሳውዝ ዳኮታ፣ቴኔሴ፣ ቴክሳስ፣ ኡታህ፣ ቬርሞንት፣ ቨርጂኒያ፣ ዋሽንግተን፣ ዌስት ቨርጂኒያ፣ ዊስኮንሲን እና ዋዮሚንግ ይጠቀሳሉ፡፡[67]

እነዚህ ግዛቶች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በተመለከተ አብዛኞቹ ቅድመ-ሁኔታዎችን አስቀምጠዋል፡፡ ቅድመ-ሁኔታዎቹ እንደግዛቶቹ የቤተሰብ ሕግጋት የተለያዩ ሲሆኑ ለአብነት የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፤ ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ከጉዲፈቻ አድራጊው ጋር ለአካለ መጠን ከመድረሱ በፊት አብሮ መኖሩ፣[68] ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ሙሉ በሙሉ የአካል ጉዳተኛ መሆን ወይም የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለበት መሆኑ፣[69] ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ከጉዲፈቻ አድራጊው ጋር ቢያንስ አስር አመት የእድሜ ልዩነት ሊኖር የሚገባው መሆኑ፣[70] ጉዲፈቻ በሚደረገው ሰውና በጉዲፈቻ አድራጊው መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና አስፈላጊነት (የእንጀራ ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ የወንድም ልጅ፣ እና የመሳሰሉት ዝምድና መኖር)[71] በሕግጋቱ ውስጥ እንደ ቅድመ-ሁኔታ ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡

ምንም እንኳ የአሜሪካ ግዛቶች ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን የሚደነግጉበት ሕግና መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች በመጠኑ የተለያዩ ቢሆኑም በአሁኑ ወቅት ሁሉም ግዛቶች ከመደበኛው ጉዲፈቻ ምንም አይነት ልዩነት ሳያደርጉ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በሕግ ፈቅደዋል፡፡[72]

### *3.2.2. እንግሊዝ*

ከአህጉረ አውሮፓ የሕግ ሥርዓት በተለየ እንደ ሌሎች የኮመን ሎው አገራት በእንግሊዝም መደበኛው ጉዲፈቻ የሕግ እውቅና ያገኘው በአንጻሩ በቅርቡ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ እንዲሁም ከአሜሪካ በተለየ የእንግሊዝ ሕግ ለአካለ መጠን ለደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሰጠው ቦታ በጣም ውስን ነው፡፡[73] ለዚህ በዋናነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በእንግሊዝ

[66] ዝኒ ከማሁ፡፡ እንዲሁም ቶማስ አዶልፍ ፓቫኖ፣ ከዚህ በላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 38፣ ገጽ 264-66 ይመለከቷል፡፡
[67] ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ድረገጽ ይመልከቱ፡ https://adoptingback.com/adopting-back/united-states-adult-adoption-law/
[68] ቨርጂኒያ
[69] ኦሀዮ፣ አላባማ
[70] ኒው ጀርሲ
[71] አሪዞና
[72] ሮበርት ኪፊ፣ ከዚህ በላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 30፣ ገጽ 1482::
[73] Kent Blore, A Gap in the Adoption Act 2009 (QLD): The Case for Allowing Adult Adoption, 10 Queensland U. Tech. L. & Just. J. 77 (2010).

በፊውዳሊዝም ላይ ተመሥርቶ የነበረው ማኅበረሰባዊ ስሪት ነው፡፡[74] በዚህ ማኅበረሰባዊ ስሪትና አስተሳሰብ መሠረት እንግሊዛዊያን መሬታቸው በደም ከሚዛመዷቸው ሰዎች በስተቀር ለሌላ ሰው በውርስ እንዲተላለፍ አይፈልጉም ነበር፡፡[75] ይህ በእንዲህ እንዳለ ጉዳዩን በተመለከተ እ.አ.አ. በ2002 ዓ.ም በወጣው ሕግ መሠረት አንድ ሰው ጉዲፈቻ ሊደረግ የሚችለው ለአካለ መጠን ከደረሰ በኋላ እስከ አንድ አመት ድረስ ማለትም አስራ ዘጠኝ አመት እስኪሞላው ድረስ ብቻ ነው፡፡[76] በተመሳሳይ መልኩ የስኮትላንድ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሚደረገው የጉዲፈቻ ማመልከቻው አስራ ስምንት አመት ከመሙላቱ በፊት የቀረበ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡[77] እነዚህን የእንግሊዝና የስኮትላንድ ሕግጋት ስንመለከት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከክልከላ ብዙም ፈቀቀ ያላለ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## 4. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ መለያ ባሕርያት

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በባሕርይው ከመደበኛው ጉዲፈቻ የተለየ ነው፡፡ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከመደበኛው ጉዲፈቻ የሚለይበት ሁለት መሠረታዊ ባሕርያት አሉ፡፡ እነሱም፦ ከጉዲፈቻው በስተጀርባ ያለው ምክንያትና የጉዲፈቻው ሂደት ሲሆኑ እንደሚከተለው ዘርዘር አድርገን እንመለከታቸዋለን፡፡

### 4.1. ከጉዲፈቻው በስተጀርባ ያለው ምክንያት (Motive)

ከዚህ በላይ በተለይም ከሮማዊያን ጉዲፈቻ ሕግ ጋር አያይዘን እንደተመለከትነው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ለማድረግ ያለው መነሻ ምክንያት በባሕርይው ከመደበኛው ጉዲፈቻ የተለየ ነው፡፡ ምንም እንኳ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ለማድረግ ያለው መነሻ ምክንያት ከመደበኛው ጉዲፈቻ የተለየ ቢሆንም እንደ ጉዲፈቻ አድራጊው ሰው ጥቅምና ፍላጎት መነሻ በማድረግ የተለያዩ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ቀደምት የአሳዳጊነት ወይም የእንጀራ እናት/አባት ግንኙነትን ወደ ሕጋዊ የወላጅና የልጅ ግንኙነት ከፍ ለማደረግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡[78] ከዚህ በተጨማሪ ዋናው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ምክንያት ተደርጎ ሊጠቀስ የሚችለው ከገንዘብ ወይም ከውርስ ጋር የተያያዘው ምክንያት ነው፡፡ ይህም ጉዲፈቻ አድራጊው ሲሞት የጉዲፈቻ ልጁ ወራሽ ሆኖ የሚቀርብበትን መንገድ ለመፍጠር ያገለግላል፡፡[79] ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ባል የሚስቱ እንዲሁም ሚስት የባሏ የሕግ ወራሽ ሆነው በማይቀርቡበት የሕግ ሥርዓት ባላቸው አገራት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ባል የሚስቱ፣ ሚስት የባሏ የሕግ ወራሽ ለማድረግ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡[80] ከዚህ በተጨማሪም በቅርብ ዘመዳሞች መካከል ለምሳሌ፣ በልጅና በወላጅ መካከል ሃብት ንብረት በውርስ ሲተላለፍ የሚከፈል ዝቅተኛ ታክስ ተጠቃሚ ለመሆን ለአካለ መጠን

[74] ቶማስ አዶልፍ ፓቫኖ፣ ከዚህ በላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 38፣ ገጽ 254፡፡
[75] ዝኒ ከማሁ፡፡
[76] የሕጉን አንቀጽ 47 ከሚከተለው ድረገጽ ላይ ይመለከቷል፤ https://www.legislation.gov.uk/ukpga/2002/38/data.pdf
[77] ኬንት ብሎር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 73፣ ገጽ 77፡፡
[78] ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 23፣ ገጽ 255::
[79] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 256፡፡
[80] ዝኒ ከማሁ፡፡ ይህ በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ የልጅና የወላጅ ግንኙነት ይፈጥራል፤ ውጤቱም በቤተዘመዳሞች መካከል የሚደርግ የግብረ ሥጋ ግኝኙነት የሚከለክል መሆኑን አንባቢ ልብ ሊለው ይገባል፡፡ ምንም እንኳ ሁሉም ግዛቶች ባያጸድቁትም እ.አ.አ. በ1994 ዓ.ም የወጣው የአሜሪካ ሞዴል የጉዲፈቻ ሕግ በባልና ሚስት መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻን የሚከለክል መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን እንደመሣሪያ የሚጠቀሙም አሉ።[81] ምንም እንኳ ይህ ምክንያት ከሕግ አውጪው ፍላጎት ያፈነገጠ ቢመስልም በተቃራኒው የፍርድ ቤት ይሁንታን ያገኘበት አጋጣሚ አለ፤ ለምሳሌ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የደልዋር ግዛት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ አንዱ ምክንያት የተፈጥሮ ልጆችን ተጠቃሚ የሚያደርገው ሃብት ንብረት በውርስ ሲተላለፍ የሚከፈል ዝቅተኛ ታክስ የጉዲፈቻ ልጆችንም ተጠቃሚ ያደርጋል በማለት ለዚህ ጥቅም እውቅና ሰጥቷል።[82] በመሆኑም ይህ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በስተጀርባ ያለው ምክንያት ጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው ቀድሞ በጉዲፈቻ ሽፋን አስበው ለማሳካት የፈለጉት ጉዳይ ይሁንም አይሁንም የሕግና የፍርድ ቤት ይሁንታ እያገኘ የመጣ መሆኑን እንገነዘባለን።

## 4.2. የጉዲፈቻው ሂደት

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከፈቀዱ አገራት ሕግጋት እንደምንረዳው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ሂደት ከመደበኛው ጉዲፈቻ የተለየ ነው። በመደበኛው ወይም ለአካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ ሂደት ውስጥ ትልቁና ዋናው ጉዳይ ጉዲፈቻው ለልጁ ጥቅም የተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ ነው። ይህ አሠራር የልጁ ጥቅም መሠረታዊ መርኅን መሠረት ያደረገ ነው። ወደ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ስንመጣ ይህንን መርኅ ማለትም ጉዲፈቻው ለጉዲፈቻ ልጁ ጥቅም መደረግ አለመደረጉን መመርመር አስፈላጊ ቢሆንም ለመርኁ የሚሰጠው ቦታና ትርጉም ግን መደበኛው ጉዲፈቻ ከሚሰጠው ቦታና ትርጉም ያነሰና የጠበበ ነው።[83]

ከጉዲፈቻ ሂደት ጋር በተለይም ከልጅ ጥቅም መሠረታዊ መርኅ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ነጥብ ከጉዲፈቻው በስተጀርባ ያለው ምክንያት ምን እንደሆነ መመርመር ነው። ምንም እንኳ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ለማድረግ በብዛት እንደ ምክንያት ቢወሰድም ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ሌሎች ለአገራዊ ፖሊሲና ለሞራል ተቃሪኒ የሆኑ ምክንያቶችም ይስተዋላሉ። ለለአካለ መጠን ከደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በስተጀርባ እነዚህ ምክንያቶች መኖር አለመኖራቸውን መመርመር ጉዳዩን በፈቀዱ አገራት በተለይም በአሜሪካ ፍርድ ቤቶች ዘንድ የተለመደ ነው። ፍርድ ቤቶች ከሚመረምሯቸው ጉዳዮች ውስጥ በሰዎቹ መካከል ያለን የግብረ ሥጋ ወይም ጾታዊ ግንኙነት ለማስቀጠል (የተቃራኒም ይሁን የተመሳሳይ ጾታ) ጉዲፈቻን በሽፋንነት ለመጠቀም መሆን አለመሆኑን እንዲሁም ሌሎች ለአገራዊ ፖሊሲ ተቃራኒ የሆኑ ጉዳዮች መኖር አለመኖራቸውን ይመረምራሉ።[84]

በጉዲፈቻ ሂደቱ ጉዲፈቻው ለጉዲፈቻ ልጁ ጥቅም መደረግ አለመደረጉን መመርመር አስፈላጊ መሥፈርት ባይሆንም ሌሎች በመደበኛው ጉዲፈቻ መሟላት ያለባቸው መሥፈርቶች ግን ለአካለ መጠን በደረሰ ሰው ጉዲፈቻም መሟላት ይኖርባቸዋል። በመደበኛው ጉዲፈቻ መሟላት ካለባቸው መሥፈርቶች ውስጥ አንዱ ነጻ ፈቃድ ሲሆን ይህ መሥፈርት ለአካለ መጠን በደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በፈቀዱ አገራት ሕግጋት ውስጥ ዋነኛው

---

[81] ዝኒ ከማሁ።
[82] In re Adoption of Swanson, 623 A.2d 1095, 1096 (Del. 1993).
[83] ብራን ኢ. ማኬብ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 39፣ ገጽ 304።
[84] ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 305-6።

መሟላት ካለባቸው መሥፈርቶች ውስጥ አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን። በመሆኑም ጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው በጉዲፈቻ ስምምነቱ ላይ ነጻ ፈቃዳቸውን ሊሰጡ ይገባል።

ነጻ ፈቃድን በተመለከተ ሊነሳ የሚችለው ሌላው ተያያዥ ነጥብ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ለምሳሌ የጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው ባል ወይም ሚስት እንዲሁም ወላጆች ጉዳይ ነው። የእነዚህ የተለያዩ ሰዎች ይሁንታ ወይም ነጻ ፈቃድ አስፈላጊነት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከጉዲፈቻው ውጤትና ከሰዎቹ የወደፊት ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው። ጉዲፈቻ ውል በመሆኑ የጉዲፈቻ አድራጊውና ተደራጊው ነጻ ፈቃድና ስምምነት አስፈላጊ ቢሆንም የጉዲፈቻ ልጁ የተፈጥሮ ወላጆች ፈቃድ እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚያስቀምጡና የማያስቀምጡ የቤተሰብ ሕግጋት አሉ።[85]

## 5. ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በፈቀዱ አገራት ከመደበኛው ጉዲፈቻ በተለየ ለተለያዩ ውስብስብ ችግሮችና ተግዳሮቶች ሲጋለጥ ይስተዋላል። በተለይ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከመፈቀዱ በፊት በሁለት ሰዎች መካከል የነበረ ግንኑነትን ወደ ሕጋዊ የጉዲፈቻ ግንኙነት በሚመጣበት ጊዜ እንዲሁም ይህ የጉዲፈቻ ግንኙነት ከተፈጠረ በኋላ የሌሎች አዳዲስ ያልነበሩ ሕግጋት መውጣት ጉዳዩን ይበልጥ ውስብስብ ሲያደርጉት ይስተዋላል። እነዚህን በተግባርና በሕግ የሚስተዋሉ ችግሮች ለመቅረፍ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ምን ምን ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት? የሚለውን ጉዳይ በዚህ ክፍል እንቃኛለን። ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻና "የልጅ መሠረታዊ ጥቅም መርህ" ፣ የእድሜ ልዩነት፣ እንዲሁም የቀደመ ግንኙነት መኖር አለመኖር ስለሚኖረው አንድምታ እና ፋይዳ ላይ ቅኝት ይደረጋል።

### 5.1. የእድሜ ልዩነት

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻን በተመለከተ የኢትዮጵያን ሕግ ጨምሮ በሌሎች አገራት ሕግጋት በጉዲፈቻ አድራጊውና ጉዲፈቻ በሚደረገው ልጅ መካካል የእድሜ ልዩነት መኖር እንዳለበት በግልጽ ተደንግጎ እናገኘዋለን። ለምሳሌ፣ በተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ መሠረት የጉዲፈቻ አድራጊው እድሜ ቢያንስ ከሃያ አምስት አመት ማነስ የለበትም፤ እንዲሁም የጉዲፈቻ ተደራጊው እድሜ ቢበዛ ከአስራ ስምንት አመት መብለጥ የለበትም።[86] በመሆኑም በጉዲፈቻ አድራጊውና በጉዲፈቻ ተደራጊው መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት በትንሹ የሰባት አመት ይሆናል ማለት ነው። ሕጉ ይህ የእድሜ ልዩነት እንዲኖር የፈለገበት ምክንያት በተፈጥሮ ልጆችና ወላጆች መካከል ሊኖር የሚችለውን የእድሜ ልዩነት በጉዲፈቻ ልጆችና ወላጆች መካከልም እንዲኖር በመፈለጉ ነው። በተፈጥሮ ልጆች በእድሜ ከወላጆቻቸው እንደሚያንሱ ሁሉ የጉዲፈቻ ልጆችም ከጉዲፈቻ አድራጊው በእድሜ ማነስ ይኖርባቸዋል። በተፈጥሮ ልጆችና ወላጆች መካከልም የሚኖረው የእድሜ ልዩነት በጉዲፈቻ

[85] ለበለጠ መረጃ Angela Chaput Foy, Adult Adoption and the Elder Population, 8 span (2006) ይመለከቷል።

[86] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ አዋጅ ቁጥር 213/1992፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ አመት፣ ልዩ እትም ቁጥር 1፣ አንቀጽ 184ና 185። በአንቀጽ 184 (2) መሠረት ጉዲፈቻ አድራጊዎቹ ባልና ሚስት ከሆኑ ከሁለቱ አንዳቸው 25 አመት ከሞላቸው በቂ መሆኑን እንገነዘባለን።

ልጆችና ወላጆች መካከል ከሌለ የልጅ እና የወላጅ ግንኙነትና ስሜት ሊፈጠር አይችልም ማለት ነው፡፡

ይህ የእድሜ ልዩነት ጉዳይ በተለይ ለአህጉረ አውሮፓ የሕግ ሥርዓት መነሻ በሆነው የሮማውያን ሕግ ተገቢ ቦታ ያገኘ ጉዳይ ነበር፡፡ የሮማዊያን ቋንቋ በነበረው በላቲኑ *adoptio naturam imitator* በአማርኛ ትርጉሙ "ጉዲፈቻ ተፈጥሮን ይመስላል" የሚለው መርኅ የእድሜ ልዩነትን ጨምሮ በጉዲፈቻ ልጅና ወላጅ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት በተፈጥሮ ልጆችና ወላጆች መካከል ካለው ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት የሚያመላክትና በውስጡ ብዙ ነጥቦችን አካቶ የያዘ መርኅ ነው፡፡[87] ይህን መርኅ አካቶ የያዘው የሮማዊያን ሕግ *"Minorem natu non posse maiorem adoptare placet: adoptio enim naturam imitatur et pro monstro est, ut major sit filius quam pater....."* በእንግሊዝኛው "It is settled that a man cannot adopt another person older than himself, for adoption imitates nature, and it would be unnatural for a son to be older than his father." የሚል ሲሆን በአማርኛ "በተፈጥሮ ልጅ ከአባቱ በእድሜ እንደማይበልጠው ሁሉ ጉዲፈቻም ከዚህ ተፈጥሮ ጋር ይመሳሰላል፤ በመሆኑም አንድ ሰው በእድሜ የሚበልጠውን ሰው ጉዲፈቻ ማድረግ አይችልም፤"[88] የሚል ተዛማጅ ትርጉም አለው፡፡ ይህ እድሜን የተመለከተው የሮማዊያን የጉዲፈቻ ሕግ በሂደት እያደገና እየዳበረ መጥቶ በጁስትንያን ሕግ በጉዲፈቻ አድራጊውና ጉዲፈቻ ተደራጊው መካከል መኖር ያለበት የእድሜ ልዩነት በትንሹ አስራ ስምንት አመት መሆን እንዳለበት ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡[89] ይህ የአስራ ስምንት አመት የእድሜ ልዩነት በዋናነት ግምት ውስጥ ያስገባው ወንዶች ለአቅመ-አዳም ደርሰው አባት ይሆኑበታል ተብሎ የታመነውና ሥነ-ሕይዎታዊ መሠረት ያለው እድሜ ነው፡፡[90] ቀደምሲል እንደተመለከትነው በሮማዊያን ሕግ በሂደት ሴቶች ጉዲፈቻ እንዲያደርጉ የተፈቀደላቸው ሲሆን ሴቶች በተፈጥሮ ከወንዶቹ ቀድመው ለአቅመ-ሄዋን ስለሚደርሱ ይህ የአስራ ስምንት አመት የእድሜ ልዩነት ሴቶችን አይመለከትም ነበር፡፡

እንደ መደበኛው ለአካለ መጠን እንዳልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ በተመሳሳይ መልኩ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን በፈቀዱ አገራት ጉዲፈቻ በሚደረገውና በጉዲፈቻ አድራጊው መካከል የእድሜ ልዩነት መኖር እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡ የዚህ ምክንያትም ልክ ለአካለ መጠን እንዳልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻ በልጆችና በወላጆች መካከል በተፈጥሮ ሊኖር የሚገባውን የእድሜ ልዩነት ለማምጣት ታስቦ ነው፡፡ ምንም እንኳ የእድሜ ልዩነት መኖር እንዳለበት ሕግጋቱ ቢደነግጉም ልዩነቱ ስንት አመት መሆን አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ግን ልዩነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ የተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶችን ብንወስድ በሕግጋቱ መካከል ያለውን ይህንን ልዩነት በግልጽ እንረዳለን፡፡ የኒው ጀርሲን ሕግ ብንመለከት የእድሜ ልዩነቱ አስር አመት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡[91] ከዚህ በተለየ የማሳቹሴትስና የኔቫዳ ሕግጋት ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ከጉዲፈቻ አድራጊው በእድሜ እስካነሰ ድረስ ጉዲፈቻ ማድረግ

---

[87] ጉዲፈቻና የእድሜ ልዩነትን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ዋልተር ጀ ዋድሊንግተን፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 12 ገጽ 392 ይመለከቷል፡፡

[88] ዝኒ ከማሁ፡፡

[89] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 395፡፡

[90] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 396፡፡

[91] Sarah Ratliff, Adult Adoption: Intestate Succession and Class Gifts under the Uniform Probate Code, 105 Nw. U. L. Rev. 1788 (2011).

እንደሚቻል ይፈቅዳሉ።[92] እነዚህ ሕግጋት ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ከጉዲፈቻ አድራጊው በወራትም ቢሆን በእድሜ እስካነሰ ድረስ ጉዲፈቻ ማድረግን እንደማይከለክሉ እንገነዘባለን። ይህ ሁኔታ ግን ቀደም ሲል የተገለጸውን ጉዲፈቻን በተፈጥሮ በልጅና በወላጅ መካከል ከሚኖረው የእድሜ ልዩነት ጋር ለማመሳሰል የሚደረገውን ጥረትና የሚኖረውን አወንታዊ ውጤት የሚጋፋ ይመስላል። ምንም እንኳ ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ከጉዲፈቻ አድራጊው በወራትና በጥቂት አመታት ማነሱ በቁጥር ደረጃ "የእድሜ ልዩነት" መኖሩ ግልጽ ቢሆንም በሁለቱ መካከል ሊኖር የሚገባው የወላጅና የልጅ ግንኙነት፣ የሥነ-ልቦና ቁርኝትና ስሜት ይኖራል ብሎ ማሰብ ግን አስቸጋሪ ነው።

## 5.2. የቀደመ የወላጅና የልጅ ግንኙነት መኖር

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የፈቀዱ አገራት በተለይም የአሜሪካ ግዛቶች የቀደመ ግንኙነትን ከመደበኛው ጉዲፈቻ በተለየ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ላይ እንደ ቅድመ-ሁኔታ ሲያስቀምጡት ይስተዋላል። በተለይም ጉዳዩ የሚቀርብላቸው የአሜሪካ ግዛት ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሕግ አውጪው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ሲፈቅድ በዋናነት ቀደምት የልጅና የወላጅ ግንኙነትን ለማስቀጠል ታሳቢ በማድረግ እንደሆነ ይጠቅሳሉ።[93] እዚህ ላይ ቀደምት የልጅና የወላጅ ግንኙነት ቅድመ-ሁኔታ በሕግ በግልጽ የተቀመጠ ሳይሆን እንደ የደለዌር ግዛት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሌሎች ጉዳዩ የቀረበላቸው ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትርጉም መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ይህ ቅድመ-ሁኔታ በዋናነት አግባብና ተፈጻሚ የሚሆነው ለማደጎና ለእንጀራ ልጆች ነው። እነዚህ የማደጎና የእንጀራ ልጆች ለአካለ መጠን ከመድረሳቸው በፊት ከጉዲፈቻ አድራጊው ጋር አብረው መኖራቸው እንደ ቅድመ-ሁኔታ ተወስዶ ጉዲፈቻው ይህንን ቀደምት ግንኙነት ወደ ልጅና ወላጅ ግንኙነት ከፍ ለማድረግና ለማስቀጠል ያገለግላል ማለት ነው። ይህ በፍርድ ቤቶች ትርጉም የተቀመጠው ቅድመ-ሁኔታ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ቀደምት የልጅና ወላጅ ግንኙነት መኖሩን ማስረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ግንኙነታቸውን ለአካለ መጠን በደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ሽፋን እንዳያስቀጥሉ ያደርጋቸዋል።[94]

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ጉዲፈቻን የፈቀዱ ሕግጋት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ በዋናነት ቀደምት የልጅና የወላጅ ግንኙነት መኖሩን እንደ መሥፈርት ይወስዳሉ። ይህ የልጅና የወላጅ ግንኙነት በተለያየ መልኩ የሚገለጽ ሲሆን ጉዲፈቻውን ለመፍቀድ እርሾ ሆኖ ያገለግላል። ነገር ግን ይህን ቀደምት የልጅና የወላጅ ግንኙነት ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን የሚፈቅዱ ሕግጋት አሉ።[95] ይህ

---

[92] ዝኒ ከማሁ።

[93] ለምሳሌ በዚህ ጉዳይ ላይ የደለዌር ግዛት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. በ1993 ዓ.ም የሚከተለውን ትንታኔ አስቀምጧል፤ *[i]ndisputably, the legislature, by providing for adoption of minors, intended to allow for the creation and formalization of parent-child relationships between nonrelated adults and children.... It is reasonable to infer that the legislature, by providing for adult adoptions, intended to allow for the formalization of the parent-child relationship where there is an existing parent-child relationship between nonrelated individuals.* ለበለጠ መረጃ ብራን ኢ. ማኬብ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 39 ይመለከቷል።

[94] ብራን ኢ. ማኬብ፣ ከዚህ በላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 39፣ ገጽ 303።

[95] Richard C. Ausness Planned Parenthood: Adult Adoption and the Right of Adoptees to Inherit, University of Kitchenery Law Faculty Scholarly Articles, 266 (2016).

ቀደምት የልጅና የወላጅ ግንኙነት የሌለበት ጉዲፈቻ ዋና አላማው ሃብትና ንብረትን በጉዲፈቻ ሰበብ በውርስ ማስተላለፍ ነው።

### 5.3. ነጻ ፈቃድ

ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ላይ ነጻ ፈቃድ ወይም ይሁንታ መስጠት ያለበት ማን ነው? የሚለውን ጉዳይ ይበልጥ ለመረዳት ከመደበኛው የልጆች ጉዲፈቻ ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ነው። ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በፈቀዱ አገራት በተለይም በአሜሪካ በመደበኛው የልጆች ጉዲፈቻ የልጁ የተፈጥሮ ወላጆች ወይም የሞግዚቶች ይሁንታና ነጻ ፈቃድ ለጉዲፈቻው አንዱ ቅድመ-ሁኔታ ሲሆን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በተመለከተ ግን በአብዛኞቹ የአሜሪካ ግዛቶች ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ይሁንታና ነጻ ፈቃድ በቂ ነው።[96] ከዚህ በተለየ ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው የተፈጥሮ ወላጆችን ፈቃድ ወይም ይሁንታ እንደ ቅድመ-ሁኔታ የሚያስቀምጡ ግዛቶች አሉ። ለምሳሌ፣ ጉዳዩ የቀረበላቸው የፍሎሪዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የጉዲፈቻ ጥያቄው ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው የተፈጥሮ ወላጆችን ፈቃድ ወይም ይሁንታ አላካተተም፤ በሚል ጉዲፈቻውን ሳያጸድቁ ውድቅ አድርገውታል።[97] በሕግጋቱ መካከል ላለው ለዚህ መሠረታዊ ልዩነት እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው ለተፈጥሮ ወላጆች ጥቅምና ስሜት የሚሰጠው ቦታ በአንድ ወገን፣ እንዲሁም ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው ለአካለ መጠን የደረሰ ስለሆነ በራሱ ጉዳይ ላይ እራሱ መወሰን ይችላል፤ የሚለው በሌላ ወገን ግምት ውስጥ የገቡና በእነዚህ መካከል ሚዛን ለማስጠበቅ የሚደረግ ጥረት ነው።

## 6. ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ አስፈላጊነትና ፋይዳ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ

ሕግ እንደ ሰው ልጅ የማኅበራዊ ባሕርይ መቆጣጠሪያ መሣሪያነቱ በጠቅላላው የጉዲፈቻ ሕግ ደግሞ በተለይ አንዴ ተደንግጎ የማይሻሻልና የማይቀየር ለዘላላም የሚኖር መድብል አለመሆኑ ግልጽ ነው። አንድ ሕግ ሲደነገግ የሚገለገልበት ማኅበረሰብ ያለበትን የፖለቲካ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እውነታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባል። ሕጉ ወጥቶ ሥራ ላይ ሲውል የነበሩት እውነታዎች በጊዜ ሂደት ሲለወጡ ሕጉ አብሮ መለወጡና መሻሻሉ የግድና አይቀሬ ነው። አንዳንዴ ደግሞ በተቃራኒው ተደንግገው ሥራ ላይ የዋሉ ሕግጋት በሆነ መልኩ ከሌሎች አገራት የተቀዱ ወይም እንዳለ የተወሰዱ ከማኅበረሰቡ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ እውነታዎችና አውድ የራቁና አብረው የማይሄዱ ሲሆኑ ይስተዋላል። ወደ ጉዲፈቻ ሕግ ስንመጣም ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው። በሌሎች አገራት እንደታየው መደበኛው የጉዲፈቻ ታሪክ ከሥነ-ሕዝብ መለኪያዎች መለዋወጥ ጋር በተለይም አሳዳጊ ከሌላቸውና ወላጅ አልባ ከሆኑ ልጆች ብዛት አኳያ፣ እንዲሁም የአገራትን የሕግና የባህል ከባቢ ሁኔታን መሠረት በማድረግ የሚታይና የሚሻሻል ነው።[98] በተመሳሳይ ከዚህ በላይ ባሉት ክፍሎች ሥር እንደተመለከትነው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን የፈቀዱ አገራት እነዚህን ሁኔታዎች በተለያየ መልኩ ግምት ውስጥ አስገብተዋል።

---

[96] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 258።
[97] ዝኒ ከማሁ።
[98] ገርን ፍራንክይስ ሚጎት፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 6፣ ገጽ 759።

አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ባይፈቅድም ሕጉ ሲወጣ ግምት ውስጥ ያላስገባቸውና የሕጉን መሻሻል የግድ የሚሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ትውፊታዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና የሕግ ምክንያቶች አሉ። እነዚህ ለቤተሰብ ሕጉ መሻሻል መነሻ የሚሆኑ የተለያዩ ተጨባጭ ምክንያቶች በዚህ ክፍል ስር ይቃኛሉ፤ ይተነተናሉ።

## 6.1. ባህላዊና ታሪካዊ መሠረት

በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመደንገግ እንደ ዋና አሳማኝ ምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ ቀደም ሲል ጉዳዩ በአገሪቱ ውስጥ ባህላዊና ታሪካዊ መሠረት ያለው መሆኑ ነው። ለዚህም ጉዳዩ በስፋት ትኩረት ተሰጥቶባቸው የነበሩትን የኦሮሞንና የአማራ ባህሎችን መመልከት በቂ ነው።

### *6.1.1. አካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በኦሮሞ ባህል ውስጥ*

በኦሮሞ ባህል ውስጥ ጉዲፈቻ ወይም ሞጋሳ በአጠቃላይ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ደግሞ በተለይ ልዩ ቦታ ተሰጥቶት እናገኘዋለን። ምንም እንኳ ጉዳዩ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የተለያየ ባህላዊና ታሪካዊ ገጽታዎች እንዲሁም ትውፊቶች ያሉት ቢሆኑም በጦርነት የተማረኩ ወይም ሰላማዊ የሆኑ ሰዎችን ማለትም ልጆችንና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ጉዲፈቻ ወይም ሞጋሳ ማድረግ በተለይ በሜጫ ኦሮሞዎች ዘንድ የተለመደ፣ የነበረና አሁንም በተወሰነ መልኩ እየተሠራበት ያለ የገዳ ሥርዓቱ አካል ነው።[99]

በኦሮሞ ባህል ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ የሚውለው ቃል "ጉዲፈቻ" የሚለው ቢሆንም ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን በተመለከተ ተገቢነት ያለው ቃል ሞጋሳ የሚለው ነው።[100] "ጉዲፈቻ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች ሲሆን፣ "ሞጋሳ" ደግሞ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ልጅ አድርጎ ለመቀበል በተለይም በሜጫና[101] በቱለማ ኦሮሞዎች ዘንድ የሚፈጸመውን ባህላዊ ሥርዓት የሚያመላክት ቃል ነው።[102] ይህም ልክ ጥንታዊ ሮማዊያን ያደርጉት እንደነበረው በኦሮሞ ባህል ለአካለ መጠን ያልደረሱና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን ለይቶ የሚያስተዳድር ባህላዊ አሠራር እንዳላቸው እንዲሁም እነዚህን ሁለት የተለየዩ ሥርዓቶች ለማመላከት ጥቅም ላይ የሚውሉ ሁለት ቃላት ጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚያመላክት ነው።[103] ለአካለ መጠን

[99] ከተባባሪ ፕሮፌሰር ፍሌ ጃለታ፣ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋና ጋዜጠኝነት ተቋም መምህር ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ።

[100] ምንም እንኳ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ትርጉም ያላቸው ቢሆንም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ጉዲፈቻ የሚለው ቃል ለአካለ መጠን ያልደረሱና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ከተፈጥሮ ወላጆቻቸው ውጪ ያሉ ሰዎች ልጅ አድርገው የሚቀበሉብትን ባህላዊ ሥርዓት ለማመላከት የገባ ቃል ነው።

[101] ከተባባሪ ፕሮፌሰር ፍሌ ጃለታ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 99።

[102] Dessalegn Negeri, GUDDIFACHAA PRACTICE AS CHILD PROBLEM INTERVENTION IN OROMO SOCIETY: THE CASE OF ADA'A LIBAN DISTRICT, A Thesis Submitted to the Research and Graduate Programs of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Social Work (MSW)፣ Addis Ababa University, 28 (2006)

[103] በጥንታዊ ሮማዊያን ዘንድ ሁለት የጉዲፈቻ አይነቶች የነበሩ ሲሆን *adoptio* የሚለው ቃል ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጉዲፈቻን ለማመላከት ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ቃል ሲሆን *adrogatio* የሚለው ቃል ደግሞ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻን ለማመላከት ይጠቀሙበት የነበረ ቃል ነው። ለበለጠ መረጃ ሀግ ሊንድሳይ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 23 ይመለከቷል።

የደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻ በስፋት ያከናውኑ ከነበሩ የኦሮሚያ አካባቢዎች የባሌና የጉጂ ኦሮሞዎች ይጠቀሳሉ። የባሌና የጉጂ ኦሮሞዎች በጦርነት የተማረከ ሰው ከማረከው ሰው ወይም ከማረከው ሰው ጎሳ ጋር እንዲኖር ይፈቀድለታል።[104]

ሞጋሳ በሁለት አይነት መንገድ የሚፈጸም ሲሆን የመጀመሪያው መንገድ ኦሮሞ ያልሆነ ሰው በገዳ ሥርዓት መሠረት የሚቀበለው ጎሳ አባል ከዚያም አልፎ የአንድ ቤተሰብ ልጅ ለመሆን በራሱ ነጻ ፈቃድ በሚያቀርበው ጥያቄ ተመስርቶ የሚፈጸም ነው።[105] ሁለተኛው መንገድ ከመጀመሪያው መንገድ የተለየና ኦሮሞ ያልሆነ/ኑ የጦር ምርኮኞችን ኦሮሞነት በማላበስ ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ጋር ለማዋሃድ የሚያገለግል ነው።[106] በኦሮሞ ባህል ሁለተኛው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የሚደረግበት መንገድ ሞጋሳ ከሚፈጸመበት የመጀመሪያው መንገድ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ማለትም በጦርነት ከተገኘ ምርኮ የተለየና የጉዲፈቻ አድራጊውንና የጉዲፈቻ ተደራጊውን ሰላማዊ ግንኙነት መሠረት ያደረገው *harmahodhaa* ወይም የጡት ማጥባት ሥርዓት ነበር። ይህ ባህላዊ ሥርዓት ይፈጸምባቸው ከነበሩ የኦሮሚያ አካባቢዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የባሌ አካባቢ አንዱ ነው።[107] በዚህ ሥርዓት ጉዲፈቻ አድራጊው አውራ ጣቱን በማርና በወተት በመንከር ጉዲፈቻ የሚደረገው ሰው እንዲጠባው ይደረጋል።[108] ይህም ተፈጥሯዊ የሆነውና ጡት በማጥባት የሚጀመረው የእናትና የልጅ ግንኙነት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል።

### 6.1.2. ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በአማራ ባህል ውስጥ

በኢትዮጵያ ባህል ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ከሚፈጸምባቸው አካባቢዎች አንዱ የአማራ ክልል ነው። በዚህ ክልል ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ብቻ ሳይሆን ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ጭምር ባህላዊ በሆነ መንገድ ልጅ አድርጎ የመቀበል ትውፊታዊ አሠራር ለረጅም ጊዜ ሲሠራበት ቆይቷል። ይህ ትውፊት በተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ስሞች የሚታወቅ ሲሆን በዋናነት ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚታዩት የማር ልጅ እና የጡት ልጅ የሚሉት መጠሪያዎች ናቸው።[109] እነዚህ መጠሪያዎች የሚያመላክቱት የሥርዓቱን አፈጻጸም ሂደትና ይዘት ነው። ቀደም ሲል በኦሮሞ ባህል የጉዲፈቻ ሥርዓት ምን እንደሚመስል እንደተመለከትነው በአማራ ባህልም ሂደቱና ሥርዓቱ ተመሳሳይ ነው።[110]

---

[104] Ayalew Duressa, Guddifachaa: Adoptioin Practice in Oromo Society with PARTICULAR Refeence to the Boranan Oromo, A Thesis Submitted in Partial Fulfilmet of the Master of Art, Addis Ababa University, 82 (2002)

[105] ከተባባሪ ፕሮፌሰር ፍሌ ጃለታ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 99።

[106] ዝኒ ከማሁ።

[107] ለበለጠ መረጃ Abebayehu Tsegaye Aredo and Dejene Gemechu Chala, *Harmahodhaa*: A Traditional Child Fostering and Fictive Kinship Formation Among the Oromo, Ethiopia, Ethiop.j.soc. lang. stud., Vol.6. No.2, (2019) ይመለከቷል።

[108] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 36-37::

[109] ለበለጠ መረጃ Birhanu Bitew, Inter-ethnic Relations Among Amhara and Kemant Ethnic Groups in North-Western Ethiopia, Int. J. Polit. Sci. Develop., (2019) እንዲሁም Solomon Addis Getahun, A History of Ethiopia's Newest Immigrants to the United States: Orphans, *Journal des africanistes*, (2011) ይመለከቷል።

[110] ዝኒ ከማሁ::

ይህ ሥርዓት በአማራ ክልል በዋናነት በሰሜን ጎንደርና ምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞኖች የተለመደ ነው፡፡[111] ከሌላ አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ አዲስ የመኖሪያ ቦት የሚመጡ ሰዎች ዘመድና ወላጅ የሚሆናቸው ሰው መፈለግ፣ ልጅ አድርገው የሚቀበሉ ሰዎችም የተፈጥሮ ልጅ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ተጨማሪ ጉልበት፣ ኃይልና መከታ የሚሆናቸው ሰው መፈለግ በእነዚህ አካባቢዎች ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ልጅ አድርጎ ከመቀበል በስተጀርባ ካሉት ምክንያቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡[112] ለአከለ መጠን የደረሱ ሰዎችን ልጅ አድርጎ የመቀበል ተግባር በተለይ በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ሰከላ፣ ደጋ ዳሞትና ወንበርማ ወረዳዎች አሁን ድረስ በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላል፡፡[113] ለምሳሌ፣ በወንበርማ ወረዳ የሚፈጸመው ጡት የማጥባት ትውፊታዊ ሥነ-ሥርዓት በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፦[114] ሥነ-ሥርዓቱ የሚፈጸመው ልጅ አድርጎ የሚቀበለው ሰው የነፍስ አባትና ሎሎች የአካባቢው ኗሪዎችና ዘመድ ወዳጆች በሚገኙበት ሲሆን ለዚህ የሚሆን ግብዣ ይዘጋጃል፡፡ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ልጅ የሚሆነው ሰው ልጅ አድርጎ የሚቀበለውን ሰው ጡት የሚጠባ ሲሆን ልጅ አድርጎ የሚቀበለው ሰው እንደ ልጁ ለመቁጠር፣ የእርሻ መሬትና ሃብት ንብረት ለመስጠት፣ በማንኛውም ጉዳይ እንደ ልጁ ለመንከባከብ እንዲሁም ሲሞት ወራሽ ሊያደርገው በነፍስ አባቱ ፊት ቃል ይገባል፡፡ ለዚህ ተግባር ግብዣ መዘጋጀቱ፣ እንዲሁም በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የነፍስ አባትና ዘመድ ወዳጅ መገኘቱ ለጉዳዩ የሚሰጠውን ክብደት ከማሳየቱም በላይ አዲስ የሚፈጠረውን የልጅና የወላጅ ግንኙነት በይፋ መጀመሩን ለማብሰር ጭምር ያገለግላል፡፡

## 6.2. ቀደምት የልጅና የአሳዳጊነት ግንኙነት እና የእንጀራ ልጅነት ግንኙነት እንዲሁም ተያያዥ ሥነ-ልቦዊ ምክንያቶች

### *6.2.1. የልጅና አሳዳጊነት ግንኙነት (Foster Care)*

በኢትዮጵያ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የውጪ አገር ዜጋ ጉዲፈቻ እንዳያደርግ መከልከሉን[115] ተከትሎ ኢትዮጵያዊያን ቤተሰቦች ልጆችን ተቀብሎ እንደ ልጅ ለማሳደግ ከፍተኛ ፍላጎትና መነሳሳት እያሳዩ ይገኛሉ፡፡[116] ወላጅ አልባ ልጆችን የመንከባከብና የማሳደግ ኃላፊነት የምዕራባዊያንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ነው፤ የሚለው ከዚህ በፊት በማኅበረሰቡ ዘንድ የነበረው አመለካከት እየተቀየረ መጥቷል፡፡[117] ምንም እንኳ በኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ልጆችን ተቀብሎ እንደ ልጅ የማሳደጉ ጉዳይ የውጪ አገር ጉዲፈቻ መከልከልን ተከትሎ ምን ያህል አድጓል፤ የሚለውን ለመመርመር ሕጉ ከወጣ አጭር ጊዜ በመሆኑ እንዲሁም ጉዳዩ ራሱን የቻለ በስታስቲክሳዊ መረጃ ላይ የተመሠረተ ጥናት መፈለጉ፣ በጉዳዩ ላይ ሳይንሳዊ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ባያስችልም ልጆችን ተቀብሎ ማሳደግ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ቤተሰቦች ዘንድ የተለመደና ለረጅም ጊዜ የቆየ አሠራር ነው፡፡

---

111 ከአቶ ደርበው ጥላሁን፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የባሕል እሴቶች ልማት ባለሙያ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ፡፡

112 ዝኒ ከማሁ፡፡

113 ዝኒ ከማሁ፡፡

114 ዝኒ ከማሁ፡፡

115 የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ማሻሻያ፣ አዋጅ ቁጥር 1070/2010፣ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 24ኛ አመት፣ ቁጥር 26 ይመለከቷል፡፡

116 ለበለጠ መረጃ Lindsay Steele, Expanding Foster Care Changing Ethiopian Communities, 2019 , https://www.mnnonline.org/news/expanding-foster-care-changing-ethiopian-communities/ ይመለከቷል፡፡

117 ዝኒ ከማሁ፡፡

እንደሚታወቀው የልጅና የአሳዳጊነት ግንኙነት ከጉዲፈቻ ግንኙነት የተለየ ነው፡፡[118] ይህ በአሳዳጊነትና በልጅነት የተጀመረው ግንኙነት በጊዜ ሂደት ልጁ ለአካለ መጠን ከደረሰ በኋላም የሚቀጥል ነው፡፡ ምንም እንኳ ግንኙነቱ ለረጅም ጊዜ የቀጠለ ቢሆንም በአሳዳጊውና ለአካለ መጠን በደረሰው ሰው መካከል ምንም አይነት የሕግ እውቅናና ውጤት የለውም፡፡[119] ይህንን ለረጅም ጊዜ የቆየ፣ በሰዎች ልብ ውስጥ የልጅና የወላጅ ግንኙነት ስሜት፣ መቀራረብ፣ መረዳዳትና ፍቅር የፈጠረ ግንኙነት ካለ ምንም ሕጋዊ ውጤት መበተን ከሰዎች ብሎም ከማኅበረሰቡ ስሜትና ፍላጎት ያፈነገጠ ይሆናል፡፡ ሕግ ለዚህና ይህንን ለመሳሰሉት ማኅበራዊና ቤተሰባዊ ችግሮች የመፍትሄ መሣሪያ በመሆኑ በአሳዳጊውና ለአካለ መጠን በደረሰ ሰው መካከል ያለን ግንኙነት የሕግ ውጤት ወዳለው የልጅና የወላጅ ግንኙነት ከፍ ማድረግ የሚቻለው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በመፍቀድ ነው፡፡

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ አሳዳጊው ልጁ ለአካለ መጠን ከመድረሱ በፊት ጉዲፈቻ ማድረግ ይችል ነበር የሚል ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ሳይፈጸም ሊቀር ይችላል፡፡ ለዚህ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የአሳዳጊው ፍላጎት ሲሆን ምንም እንኳ በሂደት የልጅና የወላጅ ስሜትና ትስስር ቢፈጠርም አሳዳጊው በወቅቱ ከአሳዳጊነት ያለፈ ሚና እንዲኖረው ላይፈልግ ይችላል፡፡ ሌላው ምክንያት ከልጁ የተፈጥሮ ወላጆች ፍላጎት ጋር የተያያዘ ሲሆን ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን የተፈጥሮ ወላጆች ፈቃዳቸውን ላይሰጡ ይችላሉ፡፡[120] በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በግልጽ እንደተመለከተው የልጁ አባትና እናት ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል፡፡[121] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በፈቀዱ አገራት ሕግጋት ከመደበኛው የልጆች ጉዲፈቻ በተለየ ለአካለ መጠን የደረሰው ሰው ወላጆች ፈቃድ እንደ ቅድመ-ሁኔታ አይቀመጥም፡፡ በመሆኑም በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች አሳዳጊው ልጁ ለአካለ መጠን ከመድረሱ በፊት ጉዲፈቻ ሳያደርገው ከቀረ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የመጨረሻው አማራጭ ይሆናል ማለት ነው፡፡

### *6.2.2. የፍቺ መበራከትና የአዲስ ጋብቻዎች መፈጠር (Divorce and the Rise of Step-Families)*

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን የፈቀዱ አገራት በብዛት እንደ-ቅድመ ሁኔታ የሚወስዱት ቀደምት የወላጅና የልጅ መሰል ግንኙነት መኖሩን ሲሆን ይህ ግንኙነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች ውስጥ ዋናው የእንጀራ አባት/እናትና የእንጀራ ልጅ ግንኙነት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፍቺን፣ በተለያዩ ምክንያቶች የጋብቻ መፍረስን፣ የቤተሰብ መለያየትንና ይህንን ተከትሎ የሚመሠረት አዲስ ጋብቻን፣ በጋብቻው ለአካለ መጠን ደርሰው ከእንጀራ አባት/እናት ጋር የሚኖሩ ሰዎችን፣ ለአካለ መጠን የደረሱ የማደጎ ልጆችን እና ይህንን የመሳሰሉ መረጃዎች የሚያዙበት፣ የሚጠናቀሩበት፣ የሚተነተኑበትና ይፋ የሚደረጉበት እንዲሁም መረጃዎቹ ለተለያዩ ጉዳዮች ጥቅም ላይ የሚውሉበት አሠራር

---

[118] በአሳዳጊነትና በጉዲፈቻ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት እንዲሁም የሕግ ውጤት ለመረዳት Anarida Delaj, Anna Schamberg, Nathalia Sosa & Camille Mendoza Soto, Adoption and Foster Care, 19 Geo. J. Gender & L. (2018). ይመለከቷል፡፡

[119] ልጁ ለአካለ መጠን ከመድረሱ በፊት አሳዳጊው ጉዲፈቻ ለማድረግ እድሉ ቢኖረውም በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ሳይፈጸም ሊቀር ይችላል፡፡

[120] Sarah Ratliff, Adult Adoption: Intestate Succession and Class Gifts under the Uniform Probate Code, 105 NW. U. L. REV. 1780 (2011).

[121] የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 86፣ አንቀጽ 191፡፡

ባለመኖሩ በጉዳዩ ላይ የተጠናቀረ መረጃ ማቅረብ አይቻልም፡፡[122] ነገር ግን እነዚህን ግንኙነቶች ማለትም ለአካለ መጠን ደርሰው ከእንጀራ አባት/እናት ጋር የሚኖሩ ሰዎችን መመልከት የተለመደ፣ የነበረና ወደፊትም የሚቀጥል ማኅበራዊና ቤተሰባዊ እውነታ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ በጉዳዩ ላይ የተሠሩ ውስን አካዳሚዊ ጥናቶችም ይህንን ያረጋግጣሉ፡፡[123]

እንደ መደበኛው ጉዲፈቻ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ቀደምት የቤተሰብ ግንኙነትን ወደ ወላጅና ልጅ ግንኙነት ከፍ ለማደረግ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፡፡[124] ይህም በተለይ ካለምንም ሕጋዊ ግንኙነት በአንድ ልጅና በአንድ ሰው መካከል የአሳዳጊነት ግንኙነት ከነበረ፣ እንዲሁም የእንጀራ ልጅና የእንጀራ አባት፣ የእንጀራ ልጅና የእንጀራ እናት ግንኙነት ካለ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ይህንን ቀደምት ግንኙነት ወደ ወላጅና ልጅ ሕጋዊ ግንኙነት ከፍ ለማድረግ አይነተኛ መሣሪያ ነው፡፡[125] ከዚህ ላይ አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባው ነጥብ በእነዚህ ግንኙነቶች ውስጥ ልጁ እድሜው ከአስራ ስምንት አመት በታች ከሆነ በመደበኛው ጉዲፈቻ አማካይነት ልጅ የሚሆንበት የሕግ መሠረት ክፍት መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በተለያዩ ምክንያቶች መደበኛውን የጉዲፈቻ አመሠራረት ሥርዓት በመጠቀም ጉዲፈቻ ሳይደረግ ቀርቶ እድሜው ከአስራ ስምንት አመት በላይ ከሆነ ይህ የሕግ አሠራር ስለማይኖር አንድ ሰው ሲያሳድገው የኖረውንና እንደ ልጁ የሚያየውን የእንጀራ ልጅ ልጁ የሚያደርግበት እድል አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ይህ አሠራር ሕግ ከሰዎች ስሜትና ፍላጎት ውጪ የሚሆንበት፣ በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን የልጅና የወላጅ ስሜት፣ ትስስር፣ ግንኙነትና ፍቅር በሕግ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ዳር ሳይደርስና ሕጋዊ መሠረት ሳይኖረው የሚቀርበትን አጋጣሚ ይፈጥራል ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህንን የመሰለ ግንኙነት በእንጀራ እናቶች/አባቶችና ለአካለ መጠን በደረሱ ሰዎች መካከል መመልከት የተለመደ የቀን ተቀን የቤተሰብ ሕይወት ነው፡፡ በዚህ ግንኙነት ተመሥርቶ የአሳዳጊዎችንና የእንጀራ አባቶችን ስም እንደ አባት ሥም ወስዶ መጠቀምም እንዲሁ የተለመደና በብዛት የሚስተዋል እውነታ ነው፡፡[126] ከዚህም አልፎ ይህንን ሁኔታ በመመልከት የአካባቢው ማኅበረሰብ እውነታውን ማለትም

---

[122] እነዚህን መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና ይፋ ማድረግ በሌሎች አገራት በተለይም በአውሮፓና አሜሪካ የተለመደ ነው፡፡ መረጃዎቹ በጉዳዩ ላይ አዲስ ፖሊሲ ለማመንጨት፣ ሕግጋትን ለመከለስና ለማሻሻል ጠቃሚ ግብአቶች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ወሳኝ ኩነቶችን ማለትም ሞት፣ልደት፣ጋብቻና ፍቺን ከነሐሴ 2008 ዓ.ም ጀምሮ መመዝገብ የተጀመረ ቢሆነም የዚህ ምርምር ፅሁፍ ትኩረት የሆነውን ማለትም በተለያዩ ምክንያቶች የጋብቻ መፍረስን ተከትሎ ከእንጀራ እናት ወይም አእንጀራ አባት ጋር የሚኖሩ ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎችን የተመለከተ የተጠናቀረ ስታስቲክሳዊ መረጃ ማግኘት አይቻልም፡፡

[123] ለምሳሌ Kasahun Amare, Phychological and Social Adjustment of Adolesenet Students Among Different Family Types, The case of Addis Ketema Senior Secondary School, A Thesis Submitted to the Graduate School of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts, (2005); Serkalem Bekle, Divorce: Its Cause and Impact on the Lives of Divorces Women and Children, A Comparative Study Between Divorced And Intact Families, A Thesis Submitted to the Graduate School of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Social Work, (2006) እንዲሁም Muleye Tarekegn, An Exploratory Research on Stepchildren's Experiences in the Stepparent Households: The Case of Kolfe Keranyo Sub-city, Addis Ababa, A Thesis Submitted to the Graduate School of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts in Social Work, (2011) ይመለከቷል፡፡

[124] ሮበርት ኪፊ፣ ከዚህ በላይ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 30፣ ገጽ 1482::

[125] ዝኒ ከማሁ፡፡

[126] ይህ ፀሀፊ ተወልዶ ባደገበት እንዲሁም አሁን በሚኖርበት አካባቢ ተመሳሳይ ሁኔታዎች መኖራቸውን ተመልክቷል፡፡

የአሳዳጊነትና የእንጀራ እናት/አባት ግንኙነት ሳይሆን ግንኙነቱ የአባት/እናትና የልጅ ግንኙነት ነው፤ ብሎ የሚቀበልበትና የሚያምንበት አጋጣሚም ብዙ ነው። ይህ ጉዳይ ግንኙነቱ በሕግ የልጅና የወላጅ እውቅና ባይሰጠውም በሰዎቹ መካከል ያለው ትስስር ምን ያህል ሥር እንደሰደደና የማኅበረሰቡን እምነትና እሳቤ እንዴት እንደቀየረ አመላካች ነው።[127] ይህ ማኅበራዊና ቤተሰባዊ ምክንያትን መሠረት ያደረገ መከራከሪያ የሕግ ድጋፍ እንዳለው ከዚህ በታች ባለው ንዑስ ክፍል ስር እንመለከታለን።

### 6.3. የቤተሰብ ሕይወት የመከበር መብት

ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ማኅበራዊ፣ ቤተሰባዊና ተያያዥ ሥነ-ልቦናዊ ምክንያቶች በተጨማሪ በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ የሚያስችል የሕግ ወይም የሰብአዊ መብት መሠረት ማንሳት ይቻላል። ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ያልፈቀዱ አገራት መንግሥታት ጉዳዩን በሕጋቸው ለመፍቀድ ሰብአዊ መብትን መሠረት ያደረገ ግዴታ አለባቸው። ይህንን አስመልክቶ ኬንት ብሎር የተባሉ ፀሀፊ መንግሥት በቤተሰብ ሕይወትና ጉዳዮች ውስጥ አላግባብ ጣልቃ እንዳይገባ የሚከለክለውንና በተለያዩ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ውስጥ እውቅና የተሰጠውን መብት መሠረት በማድረግ እንደሚከተለው ይከራከራሉ "It is submitted that the prohibition on adult adoption interferes with the human right not to be subject to arbitrary interference in family matters."[128] ይህ ክርክር በዋናነት መሠረት ያደረገው ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳንና[129] ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ ላይ ነው። በእነዚህ የሰብአዊ መብት ሰነዶች መሠረት ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ቤተሰቡ፣ መኖሪያ ቤቱ፣ የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው መልእክቶቹ አላግባብና ከሕግ ውጭ አይደፈሩም፤ ጣልቃ አይገባባቸውም።[130]

ከእነዚህ ከተዘረዘሩትና ጥበቃ ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ ለያዝነው ነጥብ አግባብነት ያለው ጉዳይ ለቤተሰብ ሕይወት የተሰጠው ጥበቃ ነው። ለቤተሰብ የተሰጠውን ይህንን ጥበቃ ለመረዳት በመጀመሪያ "ቤተሰብ" ምንድን ነው የሚለውን የቤተሰብ ትርጉም መመርመር ይገባል። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘና የቤተሰብን ትርጉም በተመለከተ ነጻ የባለሙያዎች

[127] በሁለት ሰዎች መካከል የሚፈጠር የስሜትና የሥነ-ልቦና ቁርኝት በተግባር ወደ ልጅና ወላጅ ግንኙነት የማደግ እድል አለው፤ እነዚህ ሰዎች ይህንን ግንኙነት ወደ ሕጋዊ ግንኙነት ከፍ ለማድረግ ፍላጎቱ ይኖራቸዋል በማለት ፒተር ኤን ፋውለር የተባሉ ፀሀፊ ይከራከራሉ። ለበለጠ መረጃ ፒተር ኤን ፋውለር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 40 ይመለከቷል።

[128] ኬንት ብሎር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 73፣ ገጽ 63።

[129] ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳንን እ.አ.አ. ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የተቀበለች ሲሆን ቃል-ኪዳኑ በኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፐሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 9(4) መሠረት የአገሪቱ ሕግ አካል ነው። ከዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን አንቀጽ 17 የተወሰደው የግል ሕይወት የመከበር መብት በኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፐሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ስር እውቅና የተሰጠውና ዘርዝር ብሎ የተቀመጠ ቢሆንም ይህ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ የቤተሰብ ሕይወትን በተመለከተ የሚለው ምንም ነገር የለም። በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 34 ለቤተሰብ ጥበቃ የተደረገ ቢሆንም የዚህን ድንጋጌ አርእስቱንና ዝርዝሩን ስንመለከት ጋብቻን መሠረት ያደረገ ቤተሰብንና ከዚያ የሚወለዱ ልጆችን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ይመስላል። ከዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን በተጨማሪ የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ በሂደት ዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ እየሆነ መጥቷል የሚል ክርክር ስላለ በኢትዮጵያም እንደቃልኪዳኑ አስገዳጅ የዓለም አቀፍ የሕግ ምንጭ አድርገን ልንቆጥረው እንችላለን። የዓለም አቀፉን ፍርድ ቤት ዝርዝር ስልጣንና ተግባር በሚወስነው ሕግ አንቀጽ 38 መሠረት የዓለም አቀፍ ሕግ የሕግ ምጮች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ፣ ጠቅላላ የሕግ መርኖች እንዲሁም የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ የሊቃውንት አስተምህሮዎችና ፅሁፎች መኖናቸውን ያስታውሷል።

[130] *International Covenant on Civil and Political Rights,* opened for signature 16 December 1966, 999 UNTS 171, Art. 17 (entered into force 23 March 1976); *Universal Declaration of Human Rights,* opened for signature 10 December 1948, GA Res 217A, Art. 12.

ቡድን የሆነውና የዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳንን አተገባባር የሚቆጣጠረው የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ በጠቅላላ ማብራሪያው ቁጥር 16 ጉዳዩን ተመልክቶታል፡፡ በዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል-ኪዳን አንቀጽ 17 መሠረት "ቤተሰብ" ምንድን ነው? ለሚለው የትርጉም ጥያቄ ኮሚቴው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥቷል "Regarding the term "family", the objectives of the Covenant require that for purposes of article 17 this term be given a broad interpretation to include all those comprising the family as understood in the society of the State party concerned."[131] በዚህ ማብራሪያ መሠረት ቤተሰብ ምንድን ነው? በቤተሰብ ውስጥ ማን ይኖራል? የሚሉትና መሰል የትርጉም ጥያቄዎች የሚመለሱት ጉዳዩን ማኅበረሰቡ እንዴት ይረዳዋል? የሚለውን በመመርመር ሲሆን፣ ትርጓሜውም ሰፊና ብዙ ጉዳዮችን ያካተተ መሆን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የቤተሰብ ትርጉም ለማኅበረሰቡ ከተተወ ዋናው ጥያቄ በኢትዮጵያ ማኅበረሰባዊ አውድ ዘንድ ለቤተሰብ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የሚለውን ጉዳይ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

በኢትዮጵያ በተለምዶ "ቤተሰብ" የሚለው ቃል በአንድ ቤት ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ የሰዎች ስብስብን ለማመላከት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህ የሰዎች ስብስብ ወላጆችን፣ ልጆችን፣ የእንጀራ ልጆችንና ሌሎች የቅርብ የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎችን ይጨምራል፡፡ ከዚህ በመነሳት ሦስት የቤተሰብ አይነቶችን መዘርዘር እንችላለን፡፡ እነሱም፡- እናት ወይም አባት ብቻ ከልጆቻቸው ጋር የሚኖሩበት፣ እናትና አባት ከልጆቻቸው ጋር አብረው የሚኖሩበት እንዲሁም የእንጀራ እናት ወይም አባት ከባለቤቶቻቸውና እነሱ ከሚወለዱ የእንጀራ ልጆቻቸው ጋር አብረው የሚኖሩበት ቤተሰብ ናቸው፡፡[132] በመሆኑም በሌሎች አገሮች እንደተለመደው በኢትዮጵያም ከእንጀራ አባታቸው ወይም ከእንጀራ እናታቸው ጋር የሚኖሩ ልጆችና ለአካለ መጠን የደረሱ ሰዎች በአንድ ቤተሰብ ስር ይጠቃለላሉ ማለት ነው፡፡ የቤተሰብ ትርጉም ይህንን ካካተተ ወደ ተነሳንበት የሕግ ጭብጥ ስንመለስ በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን ደርሰው ከእንጀራ አባታቸው ወይም ከእንጀራ እናታቸው ጋር የሚኖሩ ሰዎችን የእንጀራ አባታቸው ወይም የእንጀራ እናታቸው ጉዲፈቻ እንዳያደርጉ መከልከል በአንድ ቤተሰብ ሕይወት ላይ የሚደረግ አላግባብና ሕጋዊ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ነው፡፡ አንድ ሰው አብሮት የኖረውንና ያሳደገውን ለአካለ መጠን የደረሰ የእንጀራ ልጁን እንደልጁ ስለማየው ጉዲፈቻ አድርጌ ግንኙነታችን የወላጅና የልጅ ይሁን፤ ብሎ ቢከራከርና በሥራ ላይ ያለው ሕግ እድሜን መሠረት በማድረግ ብቻ ይህንን ማድረግ አትችልም ቢለው በብሎር አገላለጽ ይህ የሰብአዊ መብትን የጣሰና በቤተሰብ ሕይወት ላይ የተደረገ አላግባብ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ሲሆን ከዚያም አልፎ ቤተሰባዊ ሕይወትን እንደመበጥበጥ ሊቆጠር እንደሚችል ይህ አጥኝ ያምናል፡፡

---

[131] UNHRC, *General Comment No. 16, Para.5: Art.17*(The right to respect of privacy, family, home and correspondence, and protection of honour and reputation*)*, 32nd Sess, adopted 8 April 1988, UN Doc HRI/GEN/1/Rev.9 (Vol 1).

[132] እነዚህ ቤተሰቦች በእንግሊዝኛው single-parent family, intact family, step-parent family ይባላሉ፡፡ ለበለጠ መረጃ Kasahun Amare, Phychological and Social Adjustment of Adolesenet Students Among Different Family Types, the case of Addis Ketema Senior Secondary School, A Thesis Submitted to the Graduate School of Addis Ababa University in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Master of Arts, 21(2005) ይመልከቱ፡፡

ብሎር ከዚህ ለቤተሰባዊ ሕይወት ከተሰጠ የሰብአዊ መብት ጥበቃ በመነሳት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ለምን እንደማይፈቅድ የማስረዳት ሸክሙ በሕግ በከለከለው መንግሥት ትከሻ ላይ ይወድቃል፤ በማለት በአጽንኦት ይሞግታሉ።[133] አሁን በኢትዮጵያ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከማኅበራዊና ቤተሰባዊ እውነታዎች አኳያ፣ እንዲሁም ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች የሚመነጭ የሕግ ግዴታ ባለበት ሁኔታ፣ ከጉዳዩ ጋር የሚቃረን ተጨባጭ አገራዊ ፖሊሲና ጥቅም በሌለበት ሁኔታ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የማይፈቀድበት ምንም ምክንያት የለም፤ መንግሥትም[134] ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለምን እንደማይፈቅድ ማስረዳትና የማስረዳት ሸክሙንም መወጣት እንደማይችል የዚህ ጥናት ባለቤት ያምናል።

ለአከለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ውስጥ መንግሥት አላግባብ ጣልቃ መግባት የለበትም በማለት የሚቀርበው ሌላው ተያያዥ መከራከሪያ ከግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ክርክር በዋናነት የሚያጠነጥነው ለአከለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ከመደበኛውን የልጆች ጉዲፈቻ ጋር በማነጻጸር ነው።[135] ክርክሩ በመደበኛውን የልጆች ጉዲፈቻ ላይ መንግሥት የልጆቹን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው ሲሆን ለአከለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን በተመለከተ ግን ይህ መብት ሊኖረው አይገባም፤ ከዚያም አልፎ በጉዳዩ ጣልቃ መግባት የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ ሕገ- መንግሥታዊ መብት ጥያቄ ያስነሳል፤ ሁለት ለአካለ መጠን የደረሱና ችሎታ ያላቸው ሰዎች የልጅና የወላጅ ግንኙነት ለመፍጠር መወሰን ይችላሉ፤ የሚል ነው።[136] በመሆኑም በዚህ ክርክር መሠረት በኢትዮጵያ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ አለመፈቀዱ በኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፕሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ሥር የተደነገገውን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብትን የጣሰ ነው ብሎ መሞገት ይቻላል።[137]

## 8. የማጠቃለያ ነጥቦችና የመፍትሄ ሃሳቦች

ከጥንታዊው የሮማ ሕግ ጀምሮ ጉዲፈቻን የፈቀዱ አገራትን የጉዲፈቻ ታሪክ ስንመረምር አንድ አንኳር ነጥብ እንገነዘባለን። ይኸውም እነዚህ አገራት በጉዲፈቻ ሕጋቸው በቅድሚያ እውቅና የሰጡት ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ መሆኑን ነው። እነዚህ አገራት በሂደት ለአካለ መጠን ላልደረሱ ሰዎች ጉዲፈቻም ተገቢ የሆነና በዋናነት የልጆች ጥቅምን መሠረት ያደረጉ ሕግጋት አውጥተዋል። በኢትዮጵያም ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ጽንሰ-ሃሳብ ከመደበኛው ጉዲፈቻ ጎን ለጎን ባህላዊ በሆነ መንገድ ሲሠራበት የኖረ ነው። ይህንን ባህላዊና ትውፊታዊ አሠራር ከሌሎች ነባር የአገሪቱ የልማድ ሕግጋት ጋር ወደ ጎን በመተው ለመደበኛው የልጆች ጉዲፈቻ ብቻ እውቅና የሰጠው መሠረቱን በዋናነት ከፈረንሳይ የፍትሐ ብሔር ሕግ ያደረገው በ1952 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት

[133] ኬንት ብሎር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 73፣ ገጽ 63።

[134] “መንግሥት” የሚለው ቃል በኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፕሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50ና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎችና ሕግጋት መሠረት የፌደራል መንግሥቱንና የክልል መንግሥታትን ለመግለጽ ተመራማሪው የተጠቀመበት ቃል ነው።

[135] ፒተር ኤን ፋውለር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 40፣ ገጽ 673::

[136] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 673-74።

[137] የኢትዮጵያ ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐፕሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ።

መንግሥት የፍትሐ ብሔር ሕግ ነው፤[138] በሂደት ይህንን የፍትሐ ብሔር ሕግ ያሻሻሉ የፌደራልና የክልል የቤተሰብ ሕግጋትም የፍትሐ ብሔር ሕጉን ፈለግ ተከትለዋል። ምንም እንኳ ይህ ሕግ መሠረቱን ከፈረንሳይ ቢያደርግም ሁለቱንም ማለትም ነባሩን የኢትዮጵያ ባህልና ትውፊት እንዲሁም የፈረንሳይ ሕግ ለጉዳዩ የሰጡትን ትኩረት ወደጎን በመተው የልጆች ጉዲፈቻን ብቻ ፈቅዷል። ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ውስጥ ሳይካተት የቀረበት ምክንያት የሕጉ አርቃቂ የነበሩት ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ የውጪ አገር ዜጋ በመሆናቸው፣ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረውን ባህላዊ ጉዲፈቻ በሚገባ ለመረዳት ክፍተት መኖሩ ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ ፕሮፌሰር ዳቪድን ጨምሮ ለአርቃቂ ኮሚሽኑ አባላት የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፍርዶች መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ቀርቦላቸው የነበረ ቢሆንም፣ መጽሐፉ ወደ ፈረሳይኛ ቋንቋ ባለመተርጎሙ አርቃቂው ለጉዳዩ ጥልቅ ግንዛቤ ሳይኖራቸው የቀረ ይመስላል።[139]

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን ለመፍቀድ የሚያስችሉ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነ-ልቦናዊና የሕግ ወይም የሰብአዊ መብት ምክንያቶች አሉ። በመሆኑም እነዚህንና ሌሎች በጊዜ ሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት አሁን በሥራ ላይ ያለው የቤተሰብ ሕግ መሻሻል አለበት።[140] ተሻሽሎ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻን የሚፈቅደው የቤተሰብ ሕግ ዝርዝር ምን መሆን አለበት? የሚለው ጥያቄ ዘርፈ-ብዙ ምሁራንን በተለይም የሕግና የባህል ሊቃውንትን ያካተተ ሰፊ ጥናት ተካሂዶ በሂደት የሚመለስ ሆኖ በዋናነት ግን የጉዲፈቻ ሂደቱና ውጤቱ የአገርንና የህዝብን ጥቅም (public interest) የማይነካ፣ ከመልካም ጸባይ (morality) የማይቃረን፣ እንዲሁም የሰዎችን ድብቅ የጎንዮሽ ዓላማን ለማስፈጸም (collateral purpose) በመሣሪያነት የማያገለግል መሆን ይኖርበታል። የሚሻሻለው የጉዲፈቻ ሕግ ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በዋናነት ቀደምት ግንኙነትን መሠረት ያደረገና ይህንን ግንኙነት ወደ ወላጅና ልጅ ግንኙነት ከፍ አድርጎ ማስቀጠል የሚያስችል ሊሆን ይገባል። ብሎር "[…] adult adoptions can be permitted without opening the floodgates to adoptions of convenience"[141] በማለት በጉዳዩ ላይ እንዴት ሚዛን መጠበቅ እንደሚገባ እንደገለጹት ለአካለ መጠን ከደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ጋር

[138] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የፍትሐ ብሔር ሕግ፣አዋጅ ቁጥር 1/1952፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ በተለይ የወጣ። ይህ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 3347(1) ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ በፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ለተመለከቱት ጉዳዮች ከዚህ በፊት በልማድ ወይም ተጽፈው ይሠራባቸው የነበሩ ደንቦች ሁሉ ይህ የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለተተካ ተሽረዋል በማለት ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ ምንም እንኳ በተግባር እየተሠራበት ቢሆንም ባህላዊና ትውፊታዊ መሠረት ያለውን ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ የማድረግ ልማዳዊ አሠራርን ሽሯል ማለት ነው። ነገር ግን ይህ በተግባር የሚከናወነው ባህልንና ትውፊትን መሠረት ያደረገ አሠራር ምንም አይነት የሕግ ውጤት የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፣ በዚህ ባህላዊ አሠራር ጉዲፈቻ የተደረገ ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው እንደልጅ ስለማይቆጠር ጉዲፈቻ አድራጊው ቢሞት አይወርስም፤ እሱ ቢሞትም ጉዲፈቻ አድራጊው አይወርስም። ከዚህ በተጨማሪም ቀለብ የመስጠትና የመጠየቅ ሌሎች በወላጆችና በተወላጆች መካከል የሚኖሩ በሕግ የተደነገጉ መብቶችና ግዴታዎች አይኖሩም።

[139] ለበለጠ መረጃ John H. Beckstrom, Adoption in Ethiopia Ten Years after the Civil Code, 16 J. Afr. L. 149 (1972) ይመለከቷል።

[140] በኢትዮጵያ እነዚህን የመሰሉ አሳማኝ ምክንያቶች ሲገኙ የቤተሰብ ሕጉን በተለይም ጉዲፈቻን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ማሻሻል አዲስ ነገር አይደለም። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ ከብሔራዊ የህጻናት ፖሊሲ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1070/2010 አንቀጽ 2 መሠረት የውጭ አገር ዜጋ ጉዲፈቻ አድራጊን በተመለከተ የሚደነግጉት የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 193 ተሽሮና የአዋጁ አንቀጽ 194 (3)(መ) ተሰርዞ ነባሩ ፊደል ተራ (ሠ) ፊደል ተራ(መ) ሆኖ ተሸጋሽጓል። በሌላ አገላለጽ ይህ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የማሻሻያ አዋጅ የውጭ አገር ዜግነት ባላቸው ሰዎች የሚደረግ ጉዲፈቻን ከልክሏል።

[141] ኬንት ብሎር፣ ከዚህ በላይ ማስታወሻ ቁጥር 73፣ ገጽ 85።

ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ የጎንዮሽ ችግሮችን ግምት ውስጥ በማስገባትና ለእነዚህ ችግሮች በር በማይከፍት መልኩ አሁን በሥራ ላይ ያለውን ለአዲስ አበባና ድሬዳዋ የከተማ አስተዳደሮች የሚያገለግለው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በተለይ አንቀጽ 185 እንዲሁም የዚህ አንቀጽ የካርቦን ቅጂ የሆኑትን የክልል የቤተሰብ ሕግጋት (በተለይም ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ለአካለ መጠን የደረሰ ሰው ጉዲፈቻ ባህላዊ፣ታሪካዊና ትውፊታዊ መሠረት ያለባቸው የአማራና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች የቤተሰብ ሕግጋት) ማሻሻል ይገባል።